# የእምነት መሰረቶች ትንታኔ

በ ሸይኽ ሙሐመድ ቢን ሳሊሕ ቢን ዑሰይሚን

ተርጓሚው ሙሐመድ ጀማል ሙኽታር

አሳታሚ እስላማዊ ዳዕዋና ዕውቀት ማሕበር

# شرح أصول الإيمان



# የእምነት መሠረቶች ትንታኔ

ሸይኽ ሙሐመድ ብን ሷሊሕ ብን
አል–ዑሰይሚን

ተርጓሚ – ሙሐመድ ጀማል ሙክታር

بسم الله الرحمن الرحيم

بسم الله الرحمن الرحيم

ምሥጋና ለአላህ ይገባ። እናመሰግነዋለን። ረድኤት ከርሱ እንለምናለን። ምሕረቱንም እንጠይቀዋለን። ወደርሱ ንስሐ እንገባለን። ከነፍሳችን ክፋቶችና ከመጥፎ ሥራዎቻችንም በአላህ እንጠበቃለን። አላህ ቅኑን መንገድ የመራው ሰው የሚያጠመው የለም፣ ያጠመመውንም የሚያቀናው የለም። አጋር ከሌለው አንድ አላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን እመሰክራለሁ። ሙሐመድም መልክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ። በአክብሮት የታጀበ የአላህ እዝነትና ሠላም ለነቢዩ ለቤተሰባቸው ለባልደረቦቻቸውና በቅንነት ለተከተሏቸው ሁሉ ይድረስ።

የተውሒድ ዕውቀት ከዕውቀቶች ሁሉ የላቀና የተከበረ፣ ከሁሉም ይበልጥ ሊቀሰሙት የሚገባ ዕውቀት ነው። ስለሀያሉ አላህ ስለስሞቹ፣ ስለባህሪያቱና በፍጡራን አገልጋዮቹ ላይ ስላለው መብቱ የሚያስተምር ዕውቀት ነውና።

ወደ ሀያሉ አላህ የሚወስደው የእምነት ጉዳና መከፈቻ ቁልፍና የሕግጋቱም መሠረት ነው ተውሒድ። በዚህ ምክንያትም ከአላህ ወደ ሰው ልጆች የተላኩ ነቢያት በሙሉ በአንድ ቃል ለዚሁ ተውሒድ ጥሪ አደርገዋል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿وما أرسلنا من قبلك من رسول إلا نوحي إليه أنه لا إله إلا أنا فاعبدون.﴾ الأنبياء:٢٥

« ከአንተ በፊትም እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ፣ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢሆን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም።»[1]

1 አል–አንቢያ /21/ : 25

አላህ (ሱ.ወ) አንድ መሆኑን ለራሱ መስክሯል። መላእክቱም ሊቃውንትም እንደዚሁ ለአንድነቱ ምስክርነት ሰጥተዋል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿شهد الله أنه لا إله إلا هو، والملائكة وأولوا العلم قائما بالقسط لا إله إلا هو العزيز الحكيم﴾ آل عمران:١٨

«አላህ ፣ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲኾን፤ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ፤ መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ)፤ ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ አሸናፊው ጥበበኛው ነው።»[2]

የተውሒድ አስፈላጊነት እስከዚህ የላቀ ደረጃ ያለው እስከሆነ ድረ ስም፤ እያንዳንዱ ሙስሊም ተውሒድን ለመማርና ለማስተማር፤ በጥልቀት አስተንትኖ ለመረዳትና ለማመን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። አንድ ሙስ ሊም ሃይማኖቱን በጠነኛ መሠረት ላይ ለመገንባት፤ አስተማማኝና እርኪ እምነት ኖርት በእምነቱ ፍሬና በሚያስገኘው ውጤት ለመደሰት የተውሒድ ዕውቀት በጥልቀት ሊኖረው ይገባል።

## የእስላም ሃይማኖት

የእስላም ሃይማኖት አላህ (ሱ.ወ) ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) የላከበት፤ ሃይማ ኖቶችን ሁሉ ያጠቃለለበትና ለአገልጋዮቹ ያሟላበት፤ ጸጋውን ለሰዎች ያትረፈረፈበት ሃይማኖት ነው። ለሃይማኖትነት የወደደላቸውና ከርሱ በስተቀር ሌላ ሃይማኖት እርሱ ዘንድ ተቀባይ የማይሆን ሃይማኖት

2 አሊ- ኢምራን /3/: 18

ነው የእስላም ሃይማኖት። ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የነቢያት መደምደሚያ መሆናቸውን በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ما كان محمد أبا أحد مـن رجـالكم ولكـن رسـول اللـه وخـاتم النبيين﴾ الأحزاب:٤٠

« ሙሐመድ፤ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፤ ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፤ ...» [3]

እስላም የተሟላውና አላህ ዘንድ የተወደደ ተቀባይነት ያለው ብቸኛ ሃይማኖት መሆኑን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ اليوم أكملت لكم دينكم وأتممت عليكـم نعمتـي ورضيـت لكـم الاسلام دينا ﴾ المائدة: ٣

﴿ إن الدين عند الله الاسلام ﴾ آل عمران:١٩

﴿ ومن يبتغ غير الاسلام دينا فلن يقبل منه وهو فى الآخرة مـن الخاسرين﴾ آل عمران:٨٥

« ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም እስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፤ ... »[4]

« አላህ ዘንድ (የተወደደ) ሃይማኖት እስላም ብቻ ነው፤ ...»[5]

« ከእስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው፤ ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፤ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው።»[6]

---

3 አል–አሕዛብ /33/:40
4 አል–ማኢዳህ /5/:3
5 አሊ–ዒምራን/3/: 19
6 አሊ–ዒምራን/3/: 85

የሰው ልጆች በሙላ በእስላም ሃይማኖት እምነይነት እንዲገዙት አላህ (ሱ.ወ) ግዴታ አድርጉ ደንግጓል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ قل يا أيها الناس إني رسول الله إليكم جميعا الذى له ملك السماوات والأرض لا إله إلا هو يحيي ويميت، فآمنوا بالله ورسوله النبي الأمي الذى يؤمن بالله وكلماته، واتبعوه لعلكم تهتدون﴾ الأعراف:١٥٨

« (ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው:- እላንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደ ሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ፤ (እርሱም) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና ለርሱ ብቻ የኾነ ነው፤ እርሱ እንጂ ሌላ አምላክ የለም፤ ሕያው ያደርጋል፤ ይገድላልም፤ በአላህ፣ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የማይጽፍ የማያ ነብ ነቢይ በኾነው መልክተኛው እመኑ፤ ትመሩም ዘንድ ተከተሉት።»[7]

አቡ ሁረይራን በመጥቀስ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ውስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

( والذى نفس محمد بيده لايسمع بى أحد من هذه الأمة يهودى ولا نصرانى ثم يموت ولم يؤمن بالذى أرسلت به إلا كان من أصحاب النار)

« ነፍሴ በእጁ በሆነች (አላህ) እምላለሁ፣ ከዚህ ሕዝብ ውስተ አይሁዳዊም ይሁን ክርስትያን ስለኔ (ስለተልዕኮ) ሰምቶ፣ በተላኩበት እምነት ሳያምን የሞተ ማንኛውም ሰው ከእሳት ጓዶች (አንዱ) ይሆናል።»

---

7 አል- አዕራፍ /7/: 158

በነቢዩ ማመን ማለት ነቢዩ ያስተማሩትን ከልብ አምኖ ማረጋገጥ መቀበልና መታዘዝ ነው እንጂ እውነት ነው ብሎ መናገር ብቻ አይደለም። በዚህ ምክንያት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት የነበሩት አቡ ጧሊብ፡ ነቢዩ የተናገሩትን ሁሉ እውነት ነው ብሎ ከመናገራቸውና ሃይማኖቱ ከሁሉም ሃይማኖት በላጭ መሆኑን ከመመስከራቸውም ጋር በነቢዩ አማኝ አልነበሩም።

እስላማዊው ሃይማኖት ቀደም ሲል በነበሩት መለኮታዊ ሃይማኖቶች ውስጥ የተጠቃለሉትን ጠቃሚ ነገሮች ሙሉ በሙሉ ያካተተ ከመሆኑም በላይ፤ በተጨማሪም ለሁሉም ዘመን ሥፍራና ሕዝብ ምቹና ጠቃሚ የመሆን ብልጫ አለው። አላህ (ሱ.ወ) ለመልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላቸዋል:-

﴿ وأنزلنا إليك الكتاب بالحق مصدقا لما بين يديه من الكتاب ومهيمنا عليه﴾ المائدة: ٤٨

« ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂሲኾን በእውነት አወረድን፤ ... » 8

እስላም ለሁሉም ዘመን አገርና ሕዝብ ተስማሚና አመቺ ነው ማለት በርሱ መመሪያነት ተግባራዊ ማድረጉ በየትኛውም ዘመንና ሥፍራ የሕዝብን ጥቅም ከማስጠበቅ በስተቀር በፍጹም አይጻረርም ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ አንዳንድ ሰዎች እንደሚፈልጉት እስላም ለሁሉም ዘመን ሥፍራና ሕዝብ ያጎበድዳል ማለት አይደለም።

እስላማዊ ሃይማኖት፤ በተገቢው መንገድና በትክክል አጥብቆ የያዘውን ሰው አላህ (ሱ.ወ) ሊያግዘውና ከሌላው በላይ ሊያደርገው ቃል የገባለት እውነተኛ ሃይማኖት ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

---

8 አል–ማኢዳህ /5/: 48

﴿هو الذى أرسل رسوله بالهدى ودين الحق ليظهره على الدين كله ولو كره المشركون﴾ الصف :٩

﴿وعد الله الذين آمنوا منكم، وعملوا الصالحات ليستخلفنهم فى الأرض كما استخلف الذين من قبلهم، وليمكنن لهم دينهم الذى ارتضى لهم، وليبدلنهم من بعد خوفهم أمنا، يعبدوننى لايشركون بى شيئا، ومن كفر بعد ذلك فأولئك هم الفاسقون﴾ النور: ٥٥

« እርሱ ያ አጋሪዎች ቢጠሉም መልዕክተኛውን በመምሪያ (መጽሐፍ)፣ በውነተኛው ሃይማኖትም (በእስላምና)፣ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይቶ ሊያደርገው የላከ፣ ነው። »[9]

« አላህ እነዚያን ከናንተ ያመኑትንና መልካም ሥራዎችን የሠሩትን፣ እነዚያን ከነርሱ በፊት የነበሩትን እንደተካ በምድር ላይ በእርግጥ ሊተካቸው፣ ለነሱም ያንን የወደደላቸውን ሃይማኖታቸውን ሊያደላድልላቸው፣ ከፍርሃታቸውም በኋላ ጸጥታን ሊለውጥላቸው፣ ተስፋን ቃል ሰጥቷቸዋል፤ በኔ ምንም የማያጋሩ ኾነው ይገዙኛል፤ ከዚያም በኋላ የካደ ሰው፣ እነዚያ እነሱ አመጠኞች ናቸው።»[10]

እስላማዊው ሃይማኖት ዐቂዳና ሸሪዓ (እምነትና ድንጋጌ) ነው። በዐቂዳውም ሆነ በሸሪዓው የተሟላ ነው።

1/ የአላህን ተውሒድ (አንድነት) ያስተምራል፤ ከሽርክ (ከማጋራት) ይከለክላል።

2/ እውነት መናገርን ያዛል፤ ከውሸት ይከለክላል።

---

9 አል–ሶፍ /61/:9
10 አል– ኑር /24/: 55

3/ ፍትሕና እኩልነት እንዲሰፍን ያዛል፤ ግፍና ጭቆና ይከለክላል።[11]

4/ ለታማኝነትና ለአደራ ጠባቂነት ያዛል፤ ከካዲነትና ከእምነት አጉዳይነት ይከለክላል።

5. ለቃል ኪዳን አክባሪነት ያዛል፤ ቃለ አባይነትን ይከለክላል።

6. ለወላጆች መታዘዝና በጐአድራጊነት ያዛል፤ እነሱን ማስቀየም ይከለክላል።

7. ዝምድና እንዲቀጥል ያዛል፤ ዝምድና ማቋረጥን ይከለክላል።

8. ለመልካም ጉርብትና ያዛል፤ መጥፎ ጉርብትና ይከለክላል።

በአጠቃላይ አነጋገር እስላም በመልካም ሥነምግባራት ሁሉ ያዛል። ከመጥፎና ውዳቂ ባህርያት ሁሉ ይከለክላል።

በመልካም ተግባራት ሁሉ ያዛል፤ ከመጥፎ ተግባራት ሁሉ በጥብቅ ይከለክላል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ إن الله يأمر بالعدل والاحسان، وإيتاء ذى القربى، وينهى عن الفحشاء والمنكر والبغي يعظكم لعلكم تذكرون﴾ النحل: ٩٠

« አላህ በማስተካከል፤ በማሳመርም፤ ለዘመድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል፤ ከአስከፊም፤ (ከማመንዘር) ፤ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፤ ከመበደልም ይከለክላል፤ ትገነዘቡ ዘንድ ይገሥጻችኋል።»[12]

---

11 ፍትህ ማለት ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮችን ማስተካከል የተለያዩትን ማለያየት ነው። አንዳንድ ሰዎች የእስልምና ሃይማኖት የእኩልነት ሃይማኖት ብለው ያለገደብ በአቅነት መልኩ የሚናገሩት ዓይነት ልቅ እኩልነት አይደለም። በይዘታቸውና በተፈጥሯቸው የሚለያዩ ነገሮችን ማስተካከል እስልምና ይዞት ያለመጣውና አይፈልገውም የማይመሰገነው አርአያ እንጂ ፍትሕ አይደለም።

12 አል-ነሕል /16/: 90

# የእስላም ማዕዘናት (አርካኑል እስላም)

የእስላም ማዕዘናት ማለት ሃይማኖቱ የታነጸባቸው የማዕዘን መሠረቶች ማለት ነው። እነሱም ቀጥሎ በእብኑ ዑመር አማካይነት በተላለፈው ነቢያዊ ሐዲስ ውስጥ የተመለከቱት አምስት ማዕዘናት ናቸው።

(بني الاسلام على خمسة: على أن يوحد الله (وفي رواية) على خمس: شهادة أن لا إله إلا الله وأن محمدا عبده ورسوله، وإقام الصلاة وإيتاء الزكاة وصيام رمضان والحج) متفق عليه

« እስላም የተገነባው በአምስት ነገሮች ላይ ነው:- ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ የአላህ አገልጋይና መልክተኛው መኾናቸውን መመስከር፣ ደንቡን ጠብቆና አዘውትሮ ሶላት መስገድ፣ ዘካት መክፈል፣ የረመዷን (ወር) መጾምና ሐጅ ማድረግ ናቸው። »[13]

## 1– ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ አገልጋዩና መልክተኛው መሆናቸውን መመስከር

ይህ ቃለ ምስክር በፍጹምነትና በቁርጠኝነት በልብ አምኖ በመቀበል በአንደበት የሚገለጽ ምስክርነት ነው። በእርግጠኛነቱና በቁርጠኝነቱ የአይን እማኝነት ያህል ምስክርነት ተብሏል። ይህ ቃለ ምስክርነት ሁለት ክፍሎች ቢኖሩትም– ለአላህ ተውሒድና ለሙሐመድ መልክተኛነት የተሰጠ ሁለት

---

13 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

ዓይነት ምስክርነት ቢሆንም– እንደ አንድ ማዕዘን ብቻ ይወሰዳል። ለዚህ ምክንያቱ አንድም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአላህን መልክት የሚያስተላልፉ በመሆናቸው እርሳቸው የአላህ አገልጋይና መልክተኛው መሆናቸውን መመስከር፤ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ በማረጋገጥ የተሰጠውን ቃለ ምስክርነት የሚያሟላ በመሆኑ ነው። ወይ ደግሞ ሁለቱ ቃለ ምስክርነት ሥራዎች አላህ ዘንድ ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙና ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ዋነኛው መሠረት በመሆናቸው ነው። ለአላህ (ሱ.ወ) ፍጹም ሳይሆኑና የመልክተኛውን ፈለግ ሳይከተሉ አንድ ሥራ ትክክለኛ መሆንም ሆነ ተቀባይነት ማግኘት አይችልም። ለአላህ (ሱ.ወ) ፍጹም በመሆን ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን የመመስከሩ ሁኔታ ይረጋገጣል። የአላህን መልክተኛ በመከተልም ሙሐመድ የአላህ አገልጋይና መልክተኛው መሆና ቸውን የመመስከሩ ሁኔታ ይረጋገጣል።

ከዚህ ቃለ ምስክርነት አበይተ ጥቅሞች መካከል ልብና ነፍስን ከፍጡራን ባርነት ነጻ ማውጣትና ከነቢያት በስተቀር ለሌሎች ተከታይ ከመሆን ማላቀቅ ይገኙበታል።

## 2– ሰላትን አዘውትሮ መስገድ

ይህ ማለት አዘውትሮ በተሟላ ሁኔታ ሥነ ሥርዓቱንና ወቅቶቹን ጠብቆ በትጋት በመስገድ አላህን መገዛት ማለት ነው። ሰላት ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል የልብ (የመንፈስ) እርካታና የዐይን ማረፊያ ማግኘት፣ ከመጥፎና ከሚጠሉ ነገሮች መራቅ ይገኙበታል።

## 3– ዘካት መስጠት

ዘካት ከሚከፈልባቸው የሀብት ዓይነቶች በግዴታነት የተደነገገውን የሀብት መጠን ለሚገባቸው ክፍሎች በመስጠት አላህን (ሱ.ወ) መገዛት ነው። ከጥቅሞቹ መካከል ነፍስን ከወራዳ ባህሪ– ከንፉግነት– ማጽዳትና የእስላምና የሙስሊሞችን ችግር መቅረፍ ይገኙበታል።

## 4– የረመዳንን ወር መጾም

በረመዳን ወር ቀናት ጾምን ከሚያስገድዱ ነገሮች ራስን ቆጥቦ በመዋል አላህን መገዛት ነው። ከውጤቶቹ መካከል ራስን ለአላህ (ሱ.ወ) ውዴታ ብሎ ከሚወዱት ነገሮች መቆጠብን ማለማመድ አንዱ ነው።

## 5– የሐጅ ሥርዓተ ጸሎት ማድረስ

ይህ ደግሞ ወደ ተከበረው የመካ መስጊድ በመጓዝ የሐጅ ሥርዓተ ጸሎትን በማድረስ አላህን (ሱ.ወ) መገዛት ነው።

ከውጤቶቹ መካከል የአላህን ትዕዛዝ ለመፈጸም ሲባል ኢኮኖሚያዊና አካላዊ ጥረትና መስዋትነት የመክፈል ልምድ ማስገኘት አንዱ ነው። በዚህም ምክንያት ነው ሐጅ በአላህ (ሱ.ወ) መንገድ የሚደረግ አንድ ዓይነት ትግል (ጅሃድ) የሆነው።

እነዚህ የጠቀስናቸውና ሌሎችም ያልጠቀስናቸው የማዕዘናቱ ጥቅሞችና ውጤቶች ሕዝቡን፣ በእውነተኛ ሃይማኖት ለአላህ በፍጹምነት የሚገዛ፣ ሰዎችን በፍትህና በትክክለኛነት የሚኗኗር ንጹሕና የጠራ እስላማዊ ሕዝብ ማድረግ ያስችላሉ። ከአምስቱ የእስላም ማዕዘናት ውጭ ያሉት ሌሎች የእስላም ሕግጋት እነዚህ መሠረቶች የተቃኑ ከሆኑ የተቃኑ ይሆናሉ። የሕዝቡ አጠቃላይ አኗኗርም ሃይማኖታዊ ሁኔታዎቹ ጥሩ ሆነው ሲገኙ ይሻሻላል። ሃይማኖታዊ ጉዳዮቹ በተበላሹ መጠንም አጠቃላይ መሻሻሉ ይቀርበታል።

ይህን እንዲገለጽለት የፈለገ ሰው የሚከተለውን የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ያንብብ:-

﴿ ولو أن أهل القرى آمنوا واتقوا لفتحنا عليهم بركات من السماء والأرض، ولكن كذبوا فأخذناهم بما كانوا يكسبون. أفأمن أهل القرى أن يأتيهم بأسنا بياتا وهم نائمون، أوأمن أهل القرى أن يأتيهم بأسنا ضحى وهم يلعبون. أفأمنوا مكر الله، فلا يؤمن مكر الله إلا القوم الخاسرون﴾ الأعراف:٩٦ - ٩٩

« የከተማዎች ሰዎች ባመኑና በተጠነቀቁ ኖሮ፤ በነሱ ላይ ከሰማይም ከምድርም በረከቶችን በከፈትንላቸው ነበር፤ ግን አስተባበሉ፤ ይሠሩት በነበሩትም ኃጢአት ያዝናቸው። የከተማዎቹ ሰዎችም እነሱ የተኙ ኾነው ቅጣታችን ሌሊት ሊመጣባቸው አይፈሩምን? የከተማዎቹ ሰዎችና እነሱ የሚጫወቱ ኾነው ላሉ፤ ቅጣታችን ቀን በረፋድ ሊመጣባቸው አይፈሩምን? የአላህንም ማዘናጋት (አለመቅጣቱ በድንገት መያዙን) አይፈሩምን? የአላህንም ማዘናጋት ከከሳሪዎች ሕዝቦች በስተቀር የሚተማመን የለም። » [14]

## የእስላም ዐቂዳ መሠረቶች

ቀደም ሲል እንዳወሰነው ሁሉ የእስላም ሃይ ማኖት ዐቂዳ (እምነት) እና ሸሪዓ (ድንጋጌ) ነው። አንዳንድ ሕግጋቱን በመጠቆም የሸሪዓው መሠረት ተደርገው የሚቆጠሩ ማዕዘኖቹን አውስተናል።

የእስላማዊ ዐቂዳ መሠረቶች ደግሞ በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጻሕፍቱ፣ በመልክተኞቹ (በነቢዮቹ) በመጨረሻው (የትንሣኤ) ቀንና መልካሙም ሆነ መጥፎ በአላህ ዕውቀትና በርሱ መሻት የሚፈጸም መሆኑን በማመን ላይ ይታነጻል። የአላህ መጽሐፍ– ቁርአንና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፈለገ ሕይወት ሱንና እነዚህን የእምነት መሠረቶች አመላክተዋል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

---

14 አል–አዕራፍ /7/: 93–96

﴿ ليس البر أن تولوا وجوهكم قبل امشرق و المغرب ولكن البر من ءامن بالله، واليوم الاخر، والملائكة، والكتاب والنبيين﴾

البقرة:١٧٧

« መልካም ሥራ፣ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፤ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጽሐፍትም፣ በነቢያትም ያመነ ሰው፣... »[15]

﴿ إنا كل شيئ خلقناه بقدر، وما أمرنا إلا واحدة كلمح بالبصر﴾

القمر: ٤٩ – ٥٠

« እኛ ሁሉን ነገር በልክ ፈጠርነው። ትእዛዛችንም እንደ ዓይን ቅጽበት አንዲት (ቃል) እንጅ ሌላ አይደለም።።[16]

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መልአኩ ጅብሪል ስለኢማን በጠየቃቸው ጊዜ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውታል:-

( الايمان أن تؤمن بالله، وملائكته، وكتبه، ورسله، واليوم الآخر، وتؤمن بالقدر خيره وشره) رواه مسلم

« ኢማን ማለት በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍቱ፣ በመልክተኞቹ (በነቢያቱ)፣ በመጨረሻው (የትንሣኤ) ቀን ማመንና መልካሙም ሆነ መጥፎው በአላህ መሻትና በውሳኔው የሚከሰት መሆኑን ማመን ነው። ...» [17]

በአላህ (ሱ.ወ) ማመን

በአላህ ማመን አራት ነገሮችን ያጠቃልላል:-

15 አል-በቀራህ /2/:177
16 አል-ቀመር /54/: 49-50
17 ሙስሊም የዘገበው ሐዲስ

# አንደኛ– የአላህን (ሱ.ወ) መኖር ማመን

ተፈጥሮ፣ አእምሮ፣ ሸሪዓና ሕዋሳዊ ግንዛቤ የአላህን መኖር ያመለክታሉ።

1– የተፈጥሮ አስረጅነትን በተመለከተ ማንኛውም ፍጡር ቀዳሚ አሳቤና ትምህርት ሳይኖረው በተፈጥሮው በፈጣሪው የሚያምን ሆኖ ይፈጠራል። ከዚህ የተፈጥሮ ግዴታ ከጊዜ በኋላ የሚደርስ አጋጣሚ ነገር ካልጋረደው በስተቀር ከዚህ ሕግ የሚወጣ ሰው የለም። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንኑ በማስመልከት እንዲህ ብለዋል፦

( مامن مولود إلا يولد على الفطرة، فأبواه يهودانه أو ينصرانه أو يمجسانه) رواه البخاري.

« ማንኛውም የሚወለድ ሕጻን በተፈጥሮው አማኝ (ሙስሊም) ሆኖ ይወለዳል። ወላጆቹ ናቸው ክርስቲያን ወይም አይሁዳዊ ወይም እሳት አምላኪ (ዞሮስቲያን) እንዲሆን የሚያደርጉት።» [18]

2– ለአላህ መኖር የአእምሮን አስረጅነት በተመለከተ ደግሞ ያለፈውም ሆነ ያለው ፍጥረት የግዴታ ያስገኘውና የፈጠረው አምላክ የሚያስፈልገው መሆኑን እንረዳለን። ማንኛውም ፍጥረት ራሱን በራሱ ማስገኘት አይችልምና። በአጋጣሚም ሊፈጠር አይችልም። አንድ ነገር ራሱን በራሱ መፍጠር የማይችልበት ምክንያት ያ ነገር ከመገኘቱ በፊት ያልነበረ ነውና እንዴት ሆኖ ፈጣሪ ይሆናል?!

---

18 ሙኽተሰር [illegible]

በአጋጣሚ ሊፈጠር የማይቻልበት ምክንያት ደግሞ አንድ ድርጊት ለመከሰት የግድ አድራጊ ስለሚያስፈልግ፤ በዚህ ድንቅ ሥርዓት የተሟላ ቅንብር፤ የተራቀቀ የሳቢያዎችና የውጤቶች ረቂቅ ቅንጅትና በክስተቶች መካከል በሚስተዋለው አስደናቂ ትስስር ፍጥረት በአጋጣሚ እንዳልተገኘ በቁርጠኝነት ያረጋግጣሉ። በአጋጣሚ የሚከሰት ነገር መጀመሪያውኑ ሲከሰት ሥርዓት ባለው መንገድ እስካልሆነ ድረስ ከተገኘ በኋላ ለመቆየትና ለማደግ እንዴት ሥርዓትና ቅንጅት ሊኖረው ይችላል?!

ስለዚህም ፍጥረታት ራሳቸውን በራሳቸው ያልፈጠሩና በአጋጣሚ የተገኙ እስካልሆኑ ደግሞ የፈጠራቸውና ያስገኛቸው የዓለማት ጌታ አላህ መሆኑ ግዴታ ይሆናል። አላህ (ሱ.ወ) ይህን የአእምሮ አስረጅነትና ቁርጠኛ ማረጋገጫ ሲያወሳ እንዲህ ብሏል:-

﴿ أم خلقوا من غير شيئ أم هم الخالقون، أم خلقوا السماوات والأرض بل لا يوقنون، أم عندهم خزائن ربك أم هم المصيطرون﴾ الطور:٣٥ - ٣٧

« ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን? ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጠሩን? አይደለም፤ አያረጋግጡም።ወይስ የጌታህ ግምጃ ቤቶች እነሱ ዘንድ ናቸውን? ወይስ እነሱ አሸናፊዎች ናቸውን? »[19]

ይህም ማለት ያለ ፈጣሪ አልተፈጠሩም፤ ራሳቸውን በራሳቸውም አልፈጠሩም፤ ስለዚህም ፈጣሪያቸው የዓለማት ጌታ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) ነው ማለት ነው። ከላይ የተጠቀሱትን አንቀጾች ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲያነቡ የሰሙት ጁበይር ብን ሙጥዕም የተባሉ ባልደረባ (ሰሐቢይ) ያን ጊዜ አልሰለሙም ነበረና :- እነዚህን አንቀጾች ከነቢዩ አንደበት ሰበማ ልቤ

19 አል-ጡር /52/: 35-37

በድንጋጤና በአድናቆት ሊፈርስ ነበር፤ ያኔም ነበር እምነት ልቤ ውስጥ የተደላደለው» በማለት የተናገሩትም በዚህ እውነታ ልባቸው ስለተነካ ነበር።

ነጥቡን የሚያብራራ ምሳሌ እንስጥ። በመካከላቸው ወንዞች በሚፈሱባቸው የአትክልት ሥፍራዎች የተከበበ፡ በምንጣፎችና በአልጋዎች የተሞላና በተለያዩ ጌጣጌጦች የተሸለመ ሕንጻ ቤት አለ። ይህ ሕንጻና በውስጡ የተጠቃለሉት ግዟያዎቹ እንዲሁ በአጋጣሚ ግንም ሳይሠራቸው ድንገት የተገኙ ናቸው ብሉ አንድ ሰው ቢያወራልን ወዲያውኑ ነው የምናስተባ ብለውና ወሬውን ተራ የጅላጅልነት ወሬ አድርገን የምንቆጥረው። ታዲያ መሬትን ሰማያትን ጠፈራዊ ምህዋሮችን ያካተተው ይህ ግዙፍ ዩኒቨርስ በዚህ ድንቅና ተአምራዊ ቅንብሩ ያለ ሠሪ ያለ አድራጊ ራሱን በራሱ ያስገኘ ወይም በአጋጣሚ የተፈጠረ ሊሆን ይችላል ተብሉ ይገመታልን?!

3– ለአላህ መኖር የሸሪዓ (የመለኮታዊ ሕግ) አስረጅነትን በተመለከተ:- መለኮታዊ መጻሕፍት በሙሉ ይህንኑ ይናገራሉ። በነዚህ መለኮታዊ መጻ ሕፍት (አል–ኩቱቡ–ስ–ሰማዊያህ) ውስጥ የተካተቱት ትምህርቶች የሰዎ ችን ጥቅም ለመጠበቅ የታለሙ መሆናቸው ራሱ ጥበበኛና የፍጡራኑን ጥቅሞች በጥልቀት ዐዋቂ ከሆነ ጌታ የተላለፉ ለመሆናቸው ማስረጃ ነው። በመጻሕፍቱ ውስጥ የተጠቃለሉ ተፈጥሮያዊ እውነታዎች በነባራዊ ሁኔታ በተጨባጭ የተረጋገጡ መሆናቸውም መጻሕፍቱ የገለጿቸውን ነገሮች ማስገ ኘት በሚችል ቻይ ጌታ የተላለፉ ለመሆናቸው ማስረጃ ነው።

4– የሕዋሳዊ ግንዛቤ አስረጅነት ደግሞ ከሁለት አንጻር ነው።

አንደኛው:- አላህ (ሱ.ወ) የለማኞችን ልመና ሰምቶ ጸሎታቸውን ተቀብሉ ፍላጐታቸውን ሲያሟላላቸው ችግር ነጥሚቸው ሲግጸኑት በረድ ኤቱ ሲደርስላቸው የምንሰማና የምናየው መሆኑ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ونوحا اذ نادى من قبل فلستجبنا له﴾ الانبياء:٧٦

« ትሕገም ከዚያ በረት (ጌታውን) በጠራ ጊዜ (አስታውስ)፤ ለርሱም (ጥሪውን) ተቀበልነው፤ ...» [20]

﴿ ولذ تستعيثون ربكم فاستجاب لكم﴾ الأنفال:٩

( عن أنس بن مالك رضى الله عنه قال: إن أعرابيا دخل يوم الجمعة والنبي صلى الله عليه وسلم يخطب: فقال: ((يا رسول الله))، هلك المال، وجاع العيال، فادع الله لنا، فرفع يديه ودعا فثار السحاب أمثال الجبال فلم ينزل عن منبره حتى رأيت المطر يتحادر على لحيته. وفى الجمعة الثانية قام ذلك الاعرابي أو غيره فقال: ( هدم البناء وغرق المال فادعوا اللع لنا فرفع يديه وقال اللهم حوالينا ولاعلينا، فما يشير الى إلا انفرجت)

« ከጌታችሁ ርዳታን በፈለጋችሁ ጊዜ፤... የተቀበላችሁን፤ (አስታውሱ)።» [21]

አንድ ጁምዓ ቀን ነቢዩ (ሲ.ዐ.ወ) ኹጥባ በማድረግ ላይ እያሉ አንድ ባላገር ገባና « የአላህ መልክተኛ ሆይ! ከብትና ንብረት አለቀ፤ ልጆችም ተራቡ፤ ስለዚህ አላህ ዝናም እንዲሰጠን ጸልዩልን» አላቸው።(ነቢዩም) እጆቻቸውን ወደ ላይ ከፍ በማድረግ አላህን ለመኑና ተራራ የመሰለ ደመና መታየት ጀመረ። (ነቢዩ) ድስኩሩን (ኹጥባውን) ጨርሰው ከመንበሩ ሳይወርዱ ዝናም ጺማቸው ላይ ሲንቆረቆር አየሁ። በተከታዩ ሳምንት ጁምዓ ቀንም ያ ባላገር ሰው ራሱ ወይም ሌላ ባላገር እንደዚያው ተነሳና « የአላህ መልክተኛ ሆይ! (በዝናቡ ብዛት) ቤት ፈረሰ፤ ንብረትም ተጥለቀለቀ፤ (አላህ ዝናቡን እንዲያቆም) ለምኑልን» አላቸው። (ነቢዩም) « አላህ ሆይ! በኛ ላይ ሳይሆን በአካባቢያችን አዝንበው» አሉና ወደ አንዱ አቅጣጫ በእጃቸው ሲያመለክቱ ወዲያውኑ ደመና መጥራት ያዘ በማለት አነስ ብን ማሊክን በመጥቀስ ቡኻሪ ዘግበዋል።

20 አል–አንቢያ /21/: 76
21 አል– አንፋል/8/: 9

ጸሎቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ መሟላት ያለባቸውን መመዘኛዎች አሟልተው በፍጹምነትና በእርግጠኝነት የተግጸኑትን ሁሉ አላህ (ሱ.ወ) የሚሰግቸው የመሆኑ ጉዳይ እስከዛሬው ዘመናችንም ድረስ የሚታይ ጉዳይ ሆና እንደቀጠለ ነው።

ሁለተኛው ገጽታ ደግሞ ነቢያት በትክክል ከአላህ የተላኩ ለመሆናቸው የሚሰጣቸው ከተለምዶ ውጭ የሆነውና ተአምራት (ሙዕጅዛት) ተብሉ የሚጠራው የነቢዮች ምልክትን ሰዎች አይተዋል ወይም ሰምተዋል። ይህ የነቢዮች ታአምር ነቢዮቹን ወደ ሰው ልጆች የላካቸው አላህ (ሱ.ወ) ለመናሩ ቁርጠኛ ግስረጃ ነው። ተአምራቱ ከሰው ልጅ ችሎታ ውጭ የሆኑ አላህ ለነቢያቱ እገዛና ለተልእኮአቸው ማረጋገጫ የሰጣቸው በመሆናቸው ለሰጣቸው ጌታ ሕልውና ግስረጃነታቸው የላቀ ነው።

ለዚህ ምሳሌ ለመስጠት አላህ (ሱ.ወ) ለነቢዩ ሙሳ (ዐሰ) በበትራቸው ባህሩን እንዲመቱ ሲያዛቸው መተውት ባህሩ አሥራ ሁለት ቦታ ተከፍሎ እያንዳዱ ክፍል እንደ አንድ ትልቅ ተራራ በመሆን አሥራ ሁለት ደረቅ ማሻገሪያ መንገዶች የመፈጠራቸውን ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል። ይህንኑ ታአምራዊ ክስተት አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿ فأوحينا الى موسى أن اضرب بعصاك البحر فانفلق فكان كل فرق كالطود العظيم﴾ الشعراء:٦٢

« ወደ ሙሳም ባሕሩን በበትርህ ምታው ስንል ላክንበት፤ (መታውና) ተከፈለም፤ ከፍሉም ሁሉ እንደ ታላቅ ጋራ ኾነ።»[22]

22 አሽ-ሹዐራ/27/:62

ሁለተኛ ምሳሌ ደግሞ በአላህ ፈቃድ ሙታንን በማስነሳት ከተቀበሩበት መቃብር ያስወጡ የነበሩት የነቢዩ ዒሳ (ዐሰ) ተአምር ነው። ይህንኑ አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) ስለነቢዩ ዒሳ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وأحي الموتى بإذن الله﴾ آل عمران:٤٩

« ... በአላህም ፈቃድ... ሙታንንም አስነሳለሁ። ... »[23]

﴿ وإذ تخرج الموتى بإذني﴾ المائدة: ١١٠

« ... ሙታንንም በፈቃዴ (ከመቃብራቸው) በምታወጣ ጊዜ... »[24]

ሌላ ሦስተኛ ምሳሌ ለመስጠት ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ስለነቢይነታቸው ማረጋገጫ ተአምር ጨረቃ ሁለት ቦታ እንድትገመስ በማድረግ እንዲያሳዩዋቸው ቁረይሾች ሲጠይቋቸው ነቢዩ በእጃቸው ወደ ጨረቃ ሲያመለክቱ ሁለት ቦታ ተሰንጥቃ ሰዎች መመልከታቸውን መጥቀስ ይቻላል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿ اقتربت الساعة وانشق القمر وإن يروا آية يعرضوا ويقولوا سحر مستمر﴾ القمر: ١ - ٢

« ሰዓቲቱ (የትንሣኤ ቀን) ተቃረበች፤ ጨረቃም ተገመሰ፤ ታምርንም ቢያዩ (ከእምነት) ይዞራሉ፤ (ይህ) ዘውታሪ ድግምት ነውም ይላሉ።»[25]

---

23 አል-ዒምራን /3/: 49
24 አል-ማኢዳህ /5/: 110
25 አል-ቀመር /54/: 1-2

አላህ የመልክተኞቹን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ለነቢያቱ እንዛና ድጋፍ እንዲከሰቱ የሚያደርጋቸው እነዚህ ተአምራት ለአላህ (ሱ.ወ) መኖር ቁርጠኛ ማረጋገጫ ናቸው።

## ሁለተኛ – በአላህ ጌትነት ማመን

ይህ ማለት አላህ ባላንጣም ሆነ ረዳት የሌለው ብቸኛ ጌታ መሆኑን ማመን ማለት ነው። ጌታ ማለት ፈጣሪነት ንግሥናና አዛዥነት እንጡራ መብቱ የሆኑለት ጌታ ነው። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ألا له الخلق والأمر ﴾ الأعراف :٥٤

﴿ ذلكم الله ربكم له الملك، والذين تدعون من دونه ما يملكون من قطمير ﴾ فاطر:١٣

« ... ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የርሱ ብቻ ነው! ... »

« ... ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው! ንግሥናው የርሱ ብቻ ነው! እነዚያም ከርሱ ሌላ የምትገዟቸው! የተምር ፍሬ ሺፋን እንኳ አይኖራቸውም»

በልቡ የሚያምነውን የማይናገር እብሪተኛ ካልሆነ በስተቀር ከፍጡራን የአላህን (ሱ.ወ) ጌትነት ያስተባበለ ሰው መኖሩ አይታወቅም። ካለም ፈርዖን እንዳደረገው ዓይነት በአፉ ብቻ – ሕሊናው አለመሆኑን እየነገረው– ጌታችሁ እኔ ነኝ የሚል ዓይነት ነው የሚኖረው። ይህን የፈርዖን እብሪት ቁርአን እንደሚከተለው አስፍሯል:-

---

26 አል- አዕራፍ/7/: 54
27 ፋጢር /35/: 13

﴿أنا ربكم الأعلى﴾ النازعات:٢٤

﴿يا أيها الملأ ما علمت لكم من إله غيرى﴾ القصص:٣٨

«አለም:- እኔ ታላቁ ጌታችሁ (የበላይ አምላካችሁ) ነኝ።»[28]

«ፈርዖንም እናንተ ጭፍሮች ሆይ! ከኔ ሌላ ለናንተ አምላክን ምንም አላውቅሁም! ...»[29]

ይህ አባባሉ ግን እውነት ከልቡ እንደዚያ መሆኑን ስለሚያምን ሳይሆን ራሱን በራሱ ሊሸነግል ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿وجحدوا بها واستيقنتها أنفسهم ظلما وعلوا﴾ النمل:١٤

﴿لقد علمت ما أنزل هؤلاء إلا رب السموات والأرض بصائر وإنى لأظنك يافرعون مثبورا﴾ الاسراء:١٠٢

28 አል-ናዚዓት /79/: 24
29 አል- ቀሰስ /28/: 38

« ነፍሶቻቸውም ያረጋገጧት ሲሆኑ፤ በበደልና በኩራት በካዱ ... »[30]

« (ሙሳም) :- እነዚህን (ታምራቶች)፤ መገሰጫዎች ሲሆኑ፤ የሰማያትና የምድር ጌታ እንጂ ሌላ እንዳላወረዳቸው በእርግጥ አውቀሃል፤ እኔም ፈርዖን ሆይ፤ የምትጠፋ መሆንህን በእርግጥ እጠረጥርሃለሁ አለው። »[31]

በዚህ ምክንያትም አጋሪዎች አምልኮትን በተመለከተ ከእርሱ ጋር ባዕድ አማልክት ከመያዛቸውም ጋር የአላህን ጌትነት ግን ያረጋገጡ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ قل لمن الأرض ومن فيها إن كنتم تعلمون، سيقولون لله، قل أفلا تذكرون، قل من رب السماوات السبع ورب العرش العظيم، سيقولون لله، قل أفلا تتقون، قل من بيده ملكوت كل شيء وهو يجير ولا يجار عليه إن كنتم تعلمون، سيقولون لله قل فأنى تسحرون﴾ المؤمنون:٨٤ - ٨٩

« :- ምድርና በውስጧ ያለው ሁሉ ፤ የማን ነው? የምታውቁ ብትሆኑ ፤ (ንገሩኝ)፤ በላቸው። በእርግጥ የአላህ ነው፤ ይሉሃል፤ ታዲያ አትገሠጹምን? በላቸው :- የሰባቱ ሰማያት ጌታና የታላቁ ዐርሽ ጌታ ማን ነው? በላቸው። በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል፤ እንግዲያ አትፈሩትምን? በላቸው :- የነገሩ ሁሉ ግዛት በእጁ የሆነ፤ እርሱ የሚጠብቅ፤ በርሱ ላይ የማይጠበቅ፤ ማን ነው? የምታውቁ እንደ ሆናችሁ ፤ በእርግጥ አላህ ነው፤ ይሉሃል፤ ታዲያ እንዴት ትታለላላችሁን? በላቸው። »[32]

﴿ ولئن سألتهم من خلق السماوات والأرض ليقولن خلقهن العزيز العليم﴾ الزخرف:٩

« ሰማያትንና ምድርን ማን ፈጠራቸው ብለህ ብትጠይቃቸው፤ አሸናፊው ዐዋቂው (አላህ) በእርግጥ ፈጠራቸው ይላሉ። »[33]

---

30 አል-ነምል /27/: 24
31 አል- ኢስራእ /17/: 102
32 አል-ሙእሚኑን/23/:84-89
33 አዝ-ዙኽሩፍ /43/:9

የአላህ አዛዥነትና ጌትነት የፈጣሪነትና የደንጋጊነት ጌትነትንም ያጠቃልላል። በሻው መንገድና ጥበቡ በሚወስነው ሁኔታ የፍጥረተ ዓለሙ አስተናባሪና ፍጹማዊ ዳኛ እንደሆነ ሁሉ፣ የአምልኮ (የዕባዳ) አፈጻጸም ደንብና የበይነሰብ (ሙዓመላ) ሕጎችን ጥበቡ በሚወስነው መሠረት የሚደነግግ ብቸኛ አስተዳዳሪም ነው። ከአላህ (ሱ.ወ) ጋር የአምልኮ (የዕባዳ) ሕግን ደንጋጊ ወይም የማህበራዊ ሕይወት ግንኙነቶች አስተዳዳሪ አድርጐ ሌላ ፍጡር የያዘ ሰው በአላህ አጋርቷል፤ እምነትንም አላረጋገጠም።

## ሦስተኛ:- በአምላክነቱ ማመን

ይህ ማለት ደግሞ አጋር (ሽሪክ) የሌለው ብቸኛ አምላክ አላህ መሆኑን ማመን ማለት ነው። አምላክ ማለት ፍቅርና ክብሬታ እየሰጡት የሚያመልኩበት ነገር ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ وإلهكم إله واحد لا إله إلا هو الرحمن الرحيم﴾ البقرة:١٦٣

«አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ (እርሱ) እጅግ በጣም ርህሩህ አዛኝ ነው።»[34]

﴿ شهد الله أنه لا إله إلا هو، والملائكة، وأولوا العلم، قائما بالقسط لا إله إلا هو العزيز الحكيم﴾ آل عمران:١٨

« አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ)ሲኾን ፤ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ፤ መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም፣ (እንደዚሁ መሰከሩ)፤ ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ አሸናፊው ጥበበኛው ነው።»[35]

34 አል- በቀራህ /2/: 163
35 አሊ- ዒምራን /3/: 18

ከአላህ ጋር እንደ አምላክ ተወስደው የሚመለኩ ነገሮች ሁሉ አምላክነታቸው ውድቅና ሰው ሰራሽ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ذلك بان الله هو الحق، وان ما يدعون من دونه الباطل، ولن الله هو العلي الكبير.﴾ الحج:٦٢

« ይህ፣ አላህ እርሱ እውነት በመኾኑ፣ ከእርሱም ሌላ የሚገዙት ነገር እርሱ ፍጹም ውሸት በመኾኑ፣ አላህም እርሱ የሁሉ በላይ ታላቅ በመኾኑ ነው።» [36]

እነዚህ ባዕድ አማልክት « አማልክት» መባላቸው አምላክ የመሆን መብት አያሰጣቸውም። ላት፣ ዑዛና መናት በሚል ስያሜ በዐረቢያ ይመለኩባቸው የነበሩትን ጣዖታት አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ان هى إلا أسماء سميتموها أنتم وآباؤكم، ما أنزل الله بها من سلطان﴾ النجم:٢٣

« እነርሱ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸው ስሞች ብቻ እንጅ ምንም አይደሉም። አላህ በእርሷ (መገዛት) ምንም ማስረጃ አላወረደም፣ .. »[37]

ነቢዩ ዩሱፍ (ዐ.ሰ) ለእስር ቤት ባልደረባቸው የተናገሩት ቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው ሰፍሯል:-

﴿ الرباب متفرقون أم الله الواحد القهار، ما تعبدون من دونه إلا أسماء سميتموها أنتم وآباؤكم ما أنزل الله بها من سلطان﴾

يوسف:٣٩ – ٤٠

36 አል- ሐጅ /22/: 62
37 አል- ነጅም /53/: 23

« ... የተለያዩ (ከብር ከወርቅ ከእንጨት የተሰሩ) አምላኮች ይሻላሉን ወይስ አሸናፊው አንዱ አላህ? ከርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸውን ስሞች እንጅ አትገዙም፤ አላህ በርሷ ምንም አስረጅ አላወረደም፤ »[38]

በዚህ ምክንያት ነው ነቢዮች (ሰ.ዐ.ወ) ለሕዝቦቻቸው የሚከተለውን አቢይ ትዕዛዝ ይናገሩ የነበሩት:-

﴿ اعبدوا الله مالكم من إله غيره﴾ هود:٥٠

« ... አላህን ተገዙ፤ ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም፤ ...»[39]

አጋሪዎች ግን ይህን ትዕዛዝና ጥሪ እምቢ ብለው ከአላህ ጋር ባዕድ አማልክት ያዙ። የሐሰት አማልክቱን ከአላህ (ሱ.ወ) ጋር በማምለክና ከነርሱ እገዛና ረድኤት በመለመን ተማጸኗቸው።

ጣዖታውያን (መሸሪኮች) ለባዕድ አማልክት መገዛታቸውን ፤ አላህ (ሱ.ወ) በሁለት ሕሊናዊ ማስረጃዎች ውድቅ አድርጓል።

አንደኛው – እነዚህ ባዕድ አማልክት ምንም ዓይነት የአምላክነት መለያ የሌላቸው መሆኑ ነው። ጣዖታቱ ፍጡራን እንጂ መፍጠር የማይችሉ፤ ለሚያመልኳቸው ወገኖች ጥቅም የማይሰጡና ጉዳትም የማያስወግዱላቸው፤ ማንንም የማኖሩና የመግደል ሥልጣን የሌላቸው፤ ከሰማያትም ምንም የሌላቸውና ምንም የማይጋሩት ፍጡራን ናቸው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ واتخذوا من دونه آلهة لا يخلقون شيئا وهم يخلقون. ولا يملكون لأنفسهم ضرا ولا نفعا ولا يملكون موتا ولا حياة ولا نشورا﴾ الفرقان:٣

38 ዩሱፍ (12): 39–40
39 ሁድ (11): 50

﴿قل ادعوا الذين زعمتم من دون الله لا يملكون مثقال ذرة في السموات ولا في الأرض وما لهم فيهما من شرك، وما له منهم من ظهير ولا تنفع الشفاعة عنده إلا لمن أذن له﴾ سبأ:٢٢ – ٢٣

﴿أيشركون ما لا يخلق شيئا وهم يخلقون. ولا يستطيعون لهم نصرا ولا أنفسهم ينصرون﴾ الأعراف: ١٩١ – ١٩٢

« (ከሐዲዎች) ከርሱም ሌላ፤ ምንንም የማይፈጥሩን፤ እነርሱም የሚፈጠሩን፤ ለነፍሶቻቸውም ጉዳትን ለመከላከል ጥቅምንም ለማምጣት የማይችሉን፤ ሞትንና ሕይወትንም፤ መቀስቀስንም የማይችሉን አማልክት ያዙ።»[40]

« እነዚያን ከአላህ ሌላ (አማልክት ብላችሁ) የምትሞግቱትን ጥሩ፤ በሰማያትም በምድርም ውስጥ የብናኝ ክብደት ያክል ምንንም አይችሉም፤ ለእነርሱም በሁለቱም ውስጥ ምንም ሽርክና የላቸውም፤ ከእነርሱም ለርሱ ደጋፊ አጋዥ የለውም በላቸው።»[41]

« ምንንም የማይፈጥሩትንና እነርሱም የሚፈጠሩትን (ከአላህ) ያጋራሉን? ለእነርሱም መርዳትን የማይችሉትን፤ ነፍሶቻቸውንም የማይረዱትን፤ (ያጋ ራሉን?)።»[42]

የአማልክቱ ትክክለኛ ሁኔታ ይህን የመሰለ ከሆነ ዘንዳ በእርሱ ማምለክ የከፋ ጃሂልነትና የዘቀጠ ስህተት ነው።

ሁለተኛ– እነኛ ማሻታዎቻቸውን (ሙሽሪኮች) አላህ (ሱ.ወ) እርሱ ብቻ ፈጣሪ ጌታ የሁሉም ነገር ሥልጣን በእጁ የሆነ፤ እርሱ የማይጠበቅ ሌሎች ግን በርሱ የሚጠበቁ የሆነ ጌታ መሆኑን ያረጋግጣሉ። ይህ እውነታቸው ራሱ በአምልኮትም እርሱን ብቻ እንዲያመልኩና እንዲገዙት፤ – ጌትነቱን

40 አል– ፉርቃን /25/:3
41 ሰበእ /34/: 22–23
42 አል– አዕራፍ /7/: 191–192

እንዲረጋገጡ ሁሉ ብቸኛ አምላክነቱንም እንዲያረጋግጡ ያስገድዳቸዋል።
አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ يا أيها الناس اعبدوا ربكم الذى خلقكم والذين من قبلكم لعلكم تتقون، الذى جعلكم الأرض فراشا والسماء بناء وأنزل من السماء ماء فأخرج به من الثمرات رزقا لكم فلا تجعلوا لله أندادا وأنتم تعلمون﴾ البقرة: ٢١ – ٢٢

﴿ ولئن سألتهم من خلقهم ليقولن الله فأنى يؤفكون﴾ الزخرف: ٨٧

﴿ قل من يرزقكم من السماء والأرض أم من يملك السمع والأبصار ومن يخرج الحي من الميت ويخرج الميت من الحي ومن يدبر الأمر فسيقولون الله، فقل أفلا تتقون، فذلكم الله ربكم الحق، فماذا بعد الحق إلا الضلال فأنى تصرفون﴾ يونس: ٣١ – ٣٢

« እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን፣ እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ! (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና። (እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ፣ ሰማይንም ጣራ ያደረገ ነው! ከሰማይም፣ (ከደመና) ውሃን ያወረደ፣ በርሱም ከፍሬዎች ለናንተ ሲሳይን ያወጣ ነው! እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትሆኑ፣ ለአላህ ባላንጣ ዎችን አታድርጉ።» [43]

« ማን እንደፈጠራቸውም ብትጠይቃቸው፣ በእርግጥ አላህ ነው! ይላሉ። ታዲያ (ከእምነት) ወዴት ይዞራሉ።» [44]

« ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው? መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረ ማን ነው? ከሙትም ሕያውን፣ የሚያወጣ ከሕያውም ሙትን የሚያ ወጣስ ማን ነው? ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ ማን ነው? በላቸው! በእርግጥም አላህ ነው ይሉሃል፣ ታዲያ (ለምን ታጋራላችሁ?) አትፈሩትምን? በላቸው። ይህችሁም እውነተኛ ጌታችሁ አላህ ነው፣ ከእውነትም በኋላ ጥመት እንጂ ሌላ ምን አለ? (ከውነት) እንዴት ትዞራላችሁ?» [45]

---

43 አል- በቀራህ /2/:21 – 22
44 አል-ዙኽሩፍ /43/: 87
45 ዩኑስ /10/: 431–32

# አራተኛ – በአላህ ስሞችና በባህርያቱ ማመን

ይህ ማለት አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ ወይም በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና ውስጥ ለራሱ ያረጋገጣቸውን ስሞችና ባህርያትን ለርሱ ተገቢ በሆነ መልኩ ምንም ሳያዛቡ፣ ትርጉም አልባ ሳያደርጉ፣ ከፍጡራን ጋር ሳያመሳስሉና ትክክለኛ አኳኋናቸው እንዲህ ነው ሳይሉ ማረጋገጥ ማለት ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ولله الأسماء الحسنى فادعوه بها وذروا الذين يلحدون فى أسمائه سيجزون ما كانوا يعملون﴾الأعراف:١٨٠

﴿وله المثل الأعلى فى السماوات والأرض، وهو العزيز الحكيم﴾ النحل:٦٠

﴿ليس كمثله شيء وهو السميع البصير﴾ الشورى:١١

« ለአላህም መልካም ስሞች አሉት፤ (ስትጸልዩ) በርሷም ጥሩት፤ እነዚያንም ስሞቹን የሚያጣምሙትን ተዋቸው፤ ይሠሩት የነበሩትን ነገር በእርግጥ ይመነዳሉ።»[46]

« ... ለአላህም ታላቅ ባሕርይ አለው፤ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው።»[47]

« ... የሚመስለው ምንም ነገር የለም፤ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።»[48]

በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለት ቡድኖች ከትክክለኛው መንገድ ጠመዋል:- <u>አንደኛው ቡድን</u>– የአላህን ስሞችና ባህርያት በሙሉ ወይም በከፊል ችላ ብለው ያስተባበሉና ትርጉም አልባ ያደረጉ ወገኖች (አልሙዐጢላ) ናቸው።

---

46 አል–አዕራፍ /7/: 180
47 አል– ነሕል /16/: 60
48 አል– ሹራ /42/: 11

ይህ ቡድን ስሞቹንና ባህርያቱን አረጋግጦ መቀበሉ አላህን (ሱ.ወ) ከፍጡራን ጋር ማመሳሰልን ያስከትላል በሚል ነው የማይቀበለው። ይህ አባባል ግን በተለያዩ አንጻሮች ውድቅ ነው። ከነዚህም:-

አንደኛ– የአላህ (ሱ.ወ) ንግግር እርስ በርሱ ይቃረናል ማለትን የመሰለ የተሳሳተ ውጤት ላይ እንዲደረስ ያደርጋል። አላህ (ሱ.ወ) ስሞችና ባህርያት እንዳሉት ለራሱ አረጋግጦ ምንም ነገር እርሱን የማይመስል መሆኑን ገልጾአል። ስለዚህም ስሞቹንና ባህርያቱን አረጋግጦ መቀበሉ እርሱን ከፍጡራን ጋር ከማመሳሰል ውጤት ላይ እንዲደረስ የሚያደርግ ቢሆን ኖሮ የአላህ ንግግር እርስ በራሱ ይጋጫል፤ አንዱ ሌላውን ያስተባብላል ማለት በሆነ ነበር።

ሁለተኛ– በአንድ ስም ወይም ባህርይ ውስጥ የሁለት ነገሮች መጣመር የግድ ተመሳሳዮች እንዲሆኑ አያደርጋቸውም። ሁለት ግለሰቦች ብንወስድ ሁለቱም የሚናገር የሚሰማና የሚያይ ሰው ከመሆናቸው አንጻር አንድ ዐይነት መሆናቸውን እንረዳለን። ይህ ማለት ግን ሁለቱ ግለሰቦች የግድ በሰብእናቸው፤ ሰሚ ተመልካችና ተናጋሪ ከመሆን ባህርያቸው ሙሉ በሙሉ ይመሳሰላሉ ማለት አይደለም። እንስሳት እጆች እግሮችና ዐይኖች እንዳሏቸው እናውቃለን። በነዚህ ነገሮች አንድ ዐይነት በመሆናቸው ብቻ የግድ ተመሳሳይ እጆች እግሮችና ዐይኖች አሏቸው ማለት አይደለም።

ፍጡራን በአጠቃላይ መልኩ በሚኖራቸው የጋራ ስሞችና ባህርያት የሚለያዩ መሆናቸው ግልጽ ከሆነ ዘንዳ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል ያለው ልዩነት ከሁሉም በላይ ሰፊና ከፍተኛ ልዩነት መሆኑ ግልጽ ይሆናል።

<u>ሁለተኛው ቡድን</u>– የአመሳሳዮች (አል ሙሸብሀ) ቡድን ነው። ይህ ቡድን ደግሞ የድንጋጌ አንቀጾቹ ግልጽ ትርጉም (ኑሱስ) የሚያመለክተው ነው በሚል አባባል የአላህን ስሞችና ባህርያቱን ከፍጡራን ጋር ከማመሳሰል ጋር አረጋግጠው የሚቀበል ቡድን ነው። አላህ (ሱ.ወ) ባሮቹን የሚያናግረው መረዳትና መገንዘብ በሚችሉበት መንገድ ብቻ ነውና አንቀጾቹን የምንረዳው ከፍጡራን ስሞችና ባህርያት በማንጻር ነው የሚል አቋም አላቸው። ይህ አቋም በተለያየ አንጻር ሲታይ ውድቅና ስህተት ነው። ከነዚህም:-

አንደኛ– አላህን (ሱ.ወ) ከፍጡራት ጋር ማመሳሰል አእምሮና ሸሪዓ (ሕግ) የማይቀበለው ጉዳይ ነው። የቁርአንና የነቢዩ ሐዲስ አንቀጾች (ነሱስ) ደግሞ ውድቅ ነገር መሆን አይችሉም።

ሁለተኛ– አላህ (ሱ.ወ) ባሮቹን የሚያናግረው ከመሠረታዊ ትርጓሜው አንጻር መረዳት በሚችሉት ሁኔታ ነው። ከአጠቃላይ ትርጉሙ ውጭ የተጓላ ምንነቱንና አኳኋኑን በተመለከተ ግን ከአላህ ስሞችና ከባህርያቱ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚጠቅሱ አንቀጾች ትርጉም ፍጹማዊ ምንነትና አኳኋን የሚያውቀው አላህ ብቻ ነው።

አላህ (ሱ.ወ) ራሱን በሰሚነት ሲገልጽ፡ ሰሚነት ከአጠቃላይ ትርጉሙ አንጻር (ድምጽን መስማት ነውና) ግልጽ ነው። የአላህን (ሱ.ወ) ሰሚነት በተመለከተ ግን ትክክለኛ ትርጉሙና አኳኋኑ አይታወቅም። የመስማት ባህርይ ትክክለኛ ግንዛቤ በፍጡራን መካከል እንኳ ቢሆን የሚለያይ በመሆኑ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል ያለው የመስማት ልዩነት እጅግ የሰፋና ከፍተኛ የሆነ ፍጹማዊ ልዩነት ነው።

አላህ (ሱ.ወ) ከዐርሹ (ከዙፋኑ) በላይ መደላደሉን ሲናገር፡ መደላደል (እስትዋ) ማለት ከመሠረታዊ ትርጉሙ አንጻር ይታወቃል። የርሱን በዐርሹ ላይ መደላደል (እስትዋ) በተመለከተ ግን ትክክለኛ ምንነቱ አኳኋኑና ፍጹማዊ ትርጉሙ አይታወቅም። ፍጡራንን በተመለከተ እንኳ መደላደል የሚለው ባህርይ ይለያያልና። በወንበር ላይ መደላደልና በሚበረግግ አስቸጋሪ ግመል ጀርባ ላይ በመደላደል መካከል ግልጽ ልዩነት አለ። በፍጡራን መካከል ራሱ ልዩነት ያለው መሆኑ ከታወቀ ደግሞ በፈጣሪና በፍጡራን መደላደል መካከል ያለው ልዩነት እጅግ በጣም ሰፊና ፍጹማዊ ልዩነት ነው።

ከዚህ በላይ በገለጽነው መንገድ በአላህ (ሱ.ወ) ማመን ለምዕመናን ታላላቅ ውጤቶች የሚያስገኝ ሲሆን ከውጤቶቹ መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን:-

አንደኛ– የሚፈልጉትን ከርሱ ብቻ ለማግኘት በርሱ ብቻ ላይ ተስፋ በመጣልም ሆነ እርሱን ብቻ በመፍራት ከርሱ በስተቀር ሌላ ባለማምለክ የአላህን (ሱ.ወ) አንድነት (ተውሒድ) ማረጋገጥ፤

ሁለተኛ– ከመልካም ስሞቹና ከላቁ ባህርያቱ ጋር አንድ በሆነ አላህን በተሟላ ሁኔታ መውደድና ማክበር፤

ሦስተኛ– አላህ ያዘዘውን በመፈጸምና ከከለከለው በመታቀብ አምልኮትን (ዕባዳን) ለርሱ ብቻ ማረጋገጥ፤

## በመላእክት (በመላኢኮች) ማመን

መላእኮች በሕዋሳዊ ግንዛቤ ሥር ከሚውለው ዓለም ውጭ የሆኑ፣ አላህን የሚያገዙ ምንም ዓይነት የጌትነትና የአምላክነት ባህሪ የሌላቸው፣ አላህ (ሱ.ወ) ከብርሃን ፈጥሮአቸው ለትዕዛዞቹ በፍጹምነት የመመሪትና የመተግበር ኃይል የሰጣቸው ፍጡራን ናቸው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ومن عنده لا يستكبرون عن عبادته ولا يستحسرون، يسبحون الليل والنهار لا يفترون﴾ الأنبياء:١٩ – ٢٠

« ... እርሱ ዘንድ ያሉትም (መላእክት) እርሱን ከመገዛት አይኮሩም፣ አይሰለቹምም። በሌሊትና በቀንም ያጠሩታል፤ አያርፉም።»[49]

ቁጥራቸውንና ብዛታቸውን ከአላህ (ሱ.ወ) በስተቀር የሚያውቅ የለም። በቡኻሪና ሙስሊም ከአነስ በተዘገበው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሰማይ ዕርገት (ምዕራጅ) ሐዲስ ውስጥ እንደተረጋገጠው፣ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሰማይ ያለው የደመቀ ቤት (በይቱል መዕሙር) ተገልጾላቸው በየቀኑ እቤቱ ውስጥ ሰባ

---

49 አንቢያ /21/: 19–20

ሽህ መላእክት የሚሰግዱበት መሆኑንና እነሱ ከወጡ በኋላ ዳግም ሳይመለሱ በዚያው የሚቀሩ ሲሆን ሌላ ሰባ ሺዎች በተከታታይ የሚሰግዱበት መሆኑና ሂደቱ ለዘለዓለሙ በዚህ የሚቀጥል መሆኑን ተናግረዋል።

## በመላእክት ማመን አራት ነገሮችን ያጠቃልላል

አንደኛ– መኖራቸውን (ሕልውናቸውን) ማመን፤

ሁለተኛ– በተለይ ስማቸውን ባወቅነው እንደ ጅብሪል ባሉት ማመንና ስማቸውን በማናውቃቸው ደግሞ መኖራቸውን በአጠቃላይ ማመን፤

ሦስተኛ– በባህርያቸው (ስፋት) ያወቅናቸውን በተነገረን መሠረት ማመን፤ ጅብሪልን በተፈጥሮ ገጽታው ስድስት መቶ ክንፎች ያሉትና ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ የሞላ ሆኖ ያዩት መሆናቸውን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስለነገሩን በዚህ ማመን፤

መልአክ በአላህ (ሱ.ወ) ትዕዛዝ ወደ ወንድ ቅርጽ ሊለወጥ ይችላል። አላህ (ሱ.ወ) ጅብሪልን ወደ መርየም ሲልከው ትክክለኛ ሰው ሆኖ እንደተመሰላት ዓይነት። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከሰሐቦች ጋር እንደተቀመጡ በጣም ነጭ ልብስ የለበሰ በጣም ጥቁር ጸጉር ያለው ምንም ዓይነት የመንገደኝነት ድካም የማይታይበትና ከሰሐቦቹ መካከል ማንም የማያውቀው ሰው ዓይነት ተመስሎ መጥቶ ጉልበቱን ከነቢዩ ጉልበት አስጠግቶ መዳፎቹን በጭኖቹ ላይ አድርጎ ስለ እስላም ስለ እምነት (ኢማን) ስለደግነት (እሕሳን) ስለትንሣኤና ስለምልክቶቹ ነቢዩን ጠይቋቸዋል።

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) ምላሽ ከሰጡት በኋላ ተነስቶ ሄደ። ከሄደ በኋላ ይህ ጅብሪል ነው ሃይማኖታችሁን ሊያስተምራችሁ ነው የመጣው በማለት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሰሐቦቹ መናገራቸውን ሙስሊም ዘግበዋል።

አላህ (ሱ.ወ) ወደ ነቢዩ እብራሂምና ወደ ነቢዩ ሉጥ የላካቸው መላእክት በወንድ ሰው የተመሰሉ ነበሩ።

አራተኛ– አላህን ማፕረት (ተስቢሕ)፡ ቀንና ሌሊት ያለመሰላቸትና ያለ ድካም አላህን መገዛት የመሳሰሉ የአላህ ትዕዛዞችን የመፈጸም ተግባር የመሳሰሉ የምናውቃቸው ተግባራት እንዳላቸው ማመን፤

አንዳንዶቻቸው የተለየ ተግባር ሊኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ ጅብሪል አላህ (ሱ.ወ) ወደ ነቢያትና ወደ መልክተኞች የሚያስተላልፈውን መልእክት በታማኝነት የማድረስ ተግባር አለው።

ሚካኢል በዝናምና በዕጸዋት ጉዳይ ላይ የተመደበ ነው። እስራፊል በትንሣኤው ቀንና ሰዎች ዳግም ከሞት ተቀስቅሰው ሲነሱ መለከት በመንፋት ላይ የተመደበ ነው። መለከ ሞት ሰው ሲሞት ነፍሱን በመወሰድ ላይ የተመደበ ነው። መለከ ገሀነምም እንደዚሁ በእሳተገሐነም ላይ የተወከለ ነው። ማህጸን ውስጥ ባሉት ጽንሶች ላይ የተመደቡ መላእኮች፤ አንድ ሕጻን ተጸንሶ አራት ወር ሲሞላው አላህ (ሱ.ወ) መላእካ ይልክበትና ሲሳዩን ዕድሜውን ሥራውን መናጢ ወይም ዕድለኛ መሆኑን እንዲጽፍ ያዘዋል። የሰው ልጆችን ሥራዎች መዝግበው የሚይዙ መላእኮች፤ ለያንዳንዱ ሰው ሁለት መላእኮች ከግራና ከቀኙ ተመድበው ሥራዎቹን ይመዘግባሉ። አንድ ሰው ከተቀበረ በኋላ መቃብሩ ውስጥ ሁለት መላእኮች ጌታው ማን እንደሆን ሃይማኖቱና ነቢዩ ማን እንደሆን ይጠይቁታል። በመላእኮች ማመን ታላላቅ ውጤቶችን የሚያስገኝ ሲሆን ከነዚህም የሚከተሉት ይገኛሉ:-

<u>አንደኛ</u>– የአላህን (ሱ.ወ) ታላቅነት፤ ኃያልነቱንና ሥልጣኑን ማወቅ፤ የፍጡር ታላቅነት የፈጣሪውን ኃያልነት ያመለክታልና።

<u>ሁለተኛ</u>– አላህ (ሱ.ወ) ለሰው ልጆች የሚጠብቋቸውን፤ ሥራዎቻቸውን የሚመዘግቡና ለሌሎች ጥቅሞቻቸው የተሰለፉ መላእኮችን በመመደብ ለለገሳቸው እንክብካቤ ምሥጋና ለአላህ ማድረስ፤

<u>ሦስተኛ</u>– አላህን (ሱ.ወ) በመገዛት በሚፈጽሙት ተግባር መላእኮችን መውደድ፤

አንዳንድ ወገኖች መላእኮች አካላት መሆናቸውን አስተባብለው፡ መላእኮች በፍጥረታት ውስጥ የሰረጸ የደግነትና የከፋት መገለጫ ኃይላት

ናቸው ይላሉ። ይህ አባባል የአላህን መጽሐፍ የነቢዩን(ሰ.ዐ.ወ) ሱንና እና የሙስሊሞችን የጋራ አቋም (ኢጅማዕ) የሚያስተባብል አቋም ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ الحمد لله فاطر السموات والأرض جاعل الملائكة رسلا أولي أجنحة مثنى وثلاث ورباع﴾ فاطر:١

﴿ ولو ترى إذ يتوفى الذين كفروا الملائكة يضربون وجوههم وأدبارهم﴾ الأنفال:٥٠

﴿ ولو ترى إذ الظالمون في غمرات الموت والملائكة باسطوا أيديهم أخرجوا أنفسكم﴾ الأنعام:٩٣

« ምስጋና ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ፣መላእክትን ባለ ሁለት ሁለት፣ ባለ ሦስት ሦስትም፣ ባለ አራት አራትም ክንፎች የኾኑ መልክተኞች አድራጊ ለኾነው አላህ ይገባው፣ ...»[50]

« እነዚያንም የካዱትን፣ መላእክት ፊቶቻቸውንና ጀርባቸውን እየመቱ የቃጠሎንም ስቃይ ቅመሱ (እያሉ) በሚገድሏቸው ጊዜ ብታይ ኖሮ፣ (አስደንጋጭን ነገር ታይ ነበር)። »[51]

« ... በደለኞችንም በሞት መከራዎች ውስጥ በኾኑ ጊዜ መላእክት እጆቻቸውን ዘርጊዎች ኾነው (ለቅጣት) ነፍሶቻችሁን አውጡ፣ .. (የሚሏቸው ሲኾኑ) ብታይ ኖሮ፣ ( አስደናቂን ነገር ባየህ ነበር)።»[52]

﴿ حتى إذا فزع عن قلوبهم قالوا ماذا قال ربكم قالوا الحق، وهو العلي الكبير﴾ سبأ:٢٣

---

50 ፋጢር /35/:1
51 አል- አንፋል: 50
52 አል- አንዓም /6/:93

﴿ والملائكة يدخلون عليهم من كل باب، سلام عليكم بما صبرتم، فنعم عقبى الدار ﴾

( إذا أحب الله العبد نادى جبريل أن الله يحب فلانا فأحبه، فيحبه جبريل، فينادى جبريل فى أهل السماء، ان الله يحب فلانا فأحبوه، فيحبه أهل السماء، ثم يوضع له القبول فى الأرض)

« ከልቦቻቸው ላይ ድንጋጤው በተገለጠም ጊዜ፡ (ተማላጆቹ) ጌታችሁ ምን አለ? ይላሉ፤ (አማላጆቹ) እውነትን አለ፤ እርሱም ከፍተኛው ታላቅ ጌታ ነው፤ ይላሉ።»[53]

« ... መላእክትም በነሱ ላይ ከየደጃፉ ሁሉ ይገባሉ። ሰላም ለናንተ ይሁን (ይህ ምንዳ) በመታገሳችሁ ነው፤ የመጨረሻይቱም አገር ምን ታምር ! ይሏቸዋል።» 54

አቡ ሁረይራን በመጥቀስ ቡኻሪ በዘገቡት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ውስጥም የሚከተለውን እናገኛለን:-

« አላህ አንድ ባሪያውን ሲወድ አላህ እገሌን ይወደዋልና አንተም ውደደው በማለት ለጅብሪል ያስታውቃል፤ ጅብሪልም ይወደዋል። ጅብሪል የሰማይ ነዋሪዎችን ይጣራና አላህ እገሌን ይወደዋልና እናንተም ውደዱት ይላቸዋል። የሰማይ ነዋሪዎችም ይወዱታል። ከዚያም መሬት ላይ ተቀባይነት ያገኛል።»

« ዐርብ ቀን መጀመሪያ ለጁምዓ ሰላት ወደ መስጊድ የሚሄዱትን በቅደም ተከተላቸው መሠረት የሚመዘግቡ መላእኮች በያንዳንዱ የመስጊድ በር ላይ ይቀመጣሉ። ኢማሙ ለኹጥባ መንበር ላይ ሲቀመጥ መዝገባቸውን ይዘጉና ቁርአን (ውጻሌ) ለማዳመጥ መጥተው ይቀመጣሉ።»

እነዚህ ቁርአናዊ አንቀጾችና ነቢያዊ ሐዲሶች መላእኮች ጠማሞቹ እንሚሉት መንፈሳዊ ኃይሎች ሳይሆኑ አካላት ለመሆናቸው ግልጽ ማስረጃ ናቸው። በነዚህ አንቀጾች መሠረት ላይም ሙስሊሞች አንድ ወጥ የጋራ አቋም ወስደዋል።

---

53 ሰበእ /34/ : 23
54 አል- ረዕድ/13/ 23-24

## በመጻሕፍት (በኪታቦች) ማመን

በመጻሕፍት ማመን ማለት አላህ (ሱ.ወ) ለፍጡራን ባለው፣ርህራሄ ሰዎች ቅኑን መንገድ ተመርተው ለዛሬዋ ዓለም ሕይወትና ለነገዋ ዘለዓለ ማዊት ሕይወት ተድላ ይበቁ ዘንድ በመልክተኛ ነቢዮች አማካይነት ባስተላለፉቸው መለኮታዊ መጻሕፍት ማመን ማለት ነው።

በመጻሕፍት ማመን አራት ጉዳዮችን ያካትታል:-

አንደኛ– በትክክል ከአላህ የተወረዱ (የተላለፉ) መሆናቸውን ማመን፤

ሁለተኛ– ከነዚህ መጻሕፍት መካከል ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በተላለፈው በቁርአን፣ ለነቢዩ ሙሣ (ሰ.ዐ.ወ) በተላለፈው ተውራት (ኦሪት)፣ ለነቢዩ ዒሳ (ሰ.ዐ.ወ) በተላለፈው በእንጂል (ወንጌል) እንደ ዚሁም ለነቢዩ ዳውድ (ሰ.ዐ.ወ) በተሰጠው ዘቡር (መዝሙር) በመሳሰሉት

ስማቸውን በተለይ በምናውቀው ማመንና ስማቸውን በማናውቃቸው ደግሞ በአጠቃላይ መልኩ ማመን።

ሦስተኛ- ትክክለኛ ስነዳዊነት ያላቸውን ይዞታቸውን እንደ ቁርአን የተረጋገጠውንና ከቀደሙት መጻሕፍት መካከል ያልተለወጠውን ያልተቀየውንና ያልተከለከለውን ክፍል ማረጋገጥ።

አራተኛ- ያልተሻረ ሕግጋቱን መተግበር። ምስጢሩንና ጥቅሙን ብናውቅም ባናውቅም ወደን መቀበል። ከቁርአን በፊት የነበሩት መለኮታዊ መጻሕፍት በሙሉ በቁርአን ተሽረዋል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ وأنزلنا إليك الكتاب بالحق مصدقا لما بين يديه من الكتاب ومهيمنا عليه﴾ المائدة:٤٨

«ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በውነት አወረድን።..»[55]

ይህ ማለት ከቀደሙት መለኮታዊ መጻሕፍት ሕግጋት ውስጥ ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ በቁርአን የጸደቀ እስካልሆነ ድረስ አንዱንም ተግባራዊ ማድረግ አይፈቀድም ማለት ነው።

በመጻሕፍት ማመን ከሚያስገኛቸው ታላላቅ ውጤቶች መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን:-

አንደኛ- አላህ (ሱ.ወ) ለያንዳንዱ ሕዝብ የሚመራበት መጽሐፍ ማስተላለፉ ለፍጡራን ባሮቹ ያለውን ትኩረት ማወቅ።

---

55 አል- ማኢዳ 5/:48

ሁለተኛ– አላህ (ሱ.ወ) ለያንዳንዱ ሕዝብ ከሁኔታው ጋር የሚጣጣም መጽሐፍት በመስጠቱ ውስጥ የሚንጸባረቀውን የላቀ ጥበቡን ማወቅ፣ ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿لكل جعلنا منكم شرعة ومنهاجا﴾

« ... ከናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን፤ ...» [56]

ሦስተኛ ይህን ሁሉ ለለገሰ አላህ ምስጋና ማቅረብ፤

---

56 አል– ማኢዳ /5/: 48

# በመልክተኞች (በሩሱል) ማመን

መልክተኛ ማለት ከአላህ ዘንድ የተላለፈ ሕግን (ሸሪዓ) ለሰው ልጆች እንዲያደርስ የታዘዘ ነቢይ ነው። «ረሱል» መልክተኛ ማለት ሲሆን «ሩሱል» መልክተኞች ማለት ነው። የመጀመሪያው ረሱል ነቢዩ ኑሕ ሲሆኑ የመጨረሻው ረሱል ደግሞ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿إنا أوحينا إليك الكتاب، كما أوحينا إلى نوح والنبيين من بعده﴾ النساء: ١٦٣

« እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደነበሩት ነቢያት እንዳወረድን፣ ወደ አንተም አወረድን፣ ...»[57]

ቡኻሪ አነስ ብን ማሊክን ጠቅሰው በዘገቡት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ውስጥም የሚከተለውን እናገኛለን:-

---

57:አል–ኒሳእ /4/:163

( أن النبي صلى الله عليه وسلم ذكر ان الناس يأتون إلى ادم ليشفع لهم فيعتذر إليهم، ويقول: ائتوا نوحا اول رسول بعثه الله...)

«በትንሣኤው ቀን ሰዎች አላህን እንዲያማልዱላቸው ወደ አደም ሲመጡ አለመቻላቸውን ይቅርታ ይጠይቁና አላህ መልክተኛ (ረሱል) አድርጎ መጀመሪያ ወደ ላካቸው ወደ ኑሕ ሂዱ ይላሉ፤ ...»

ነቢዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) የነቢዮች መደምደሚያ መሆናቸውን ሲገልጽ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ما كان محمد أبا أحد من رجالكم ولكن رسول الله وخاتم النبيين﴾ الأحزاب:٤٠

« ሙሐመድ፤ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፤ ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፤ ...» [57]

ራሱን የቻለ ሕግ (ሸሪዓ) ይዞ ከአላህ (ሱ.ወ) የሚላክ መልክተኛ (ረሱል) የሌለው ሕዝብ አልነበረም። ወይም ከበፊቱ የነበረውን ሕግ (ሸሪዓ) እንዲያድስ ከአላህ የሚታዘዝ ነቢይ ያልነበረው ሕዝብ የለም።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ولقد بعثنا في كل أمة رسولا، ان اعبدوا الله، واجتنبوا الطاغوت﴾ النحل:٣٦

﴿ وإن من أمة إلا خلا فيها نذير﴾ فاطر: ٢٤

---

57 አል- አሕዛብ /33/ 40

﴿ إنا أنزلنا التوراة فيها هدى ونور، يحكم بها النبيون الذين أسلموا للذين هادوا ﴾ المائدة::

« በየሕዝቦችም ሁሉ ውስጥ፡ አላህን ተገዙ፡ ጣዖትንም ራቁ፡ በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል፡ ...» [58]

« ... ማንኛይቱም ሕዝብ በውስጧ አስፈራሪ ያላለፈባት የለችም።» [59]

« እኛ ተውራትን በውስጧ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድን፤ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በነዚያ ይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዱሉ፤..» [60]

መልክተኞች (ሩሱል) ምንም ዓይነት የጌትነትም ሆነ የአምላክነት መለያ የሌላቸው ሰብዓዊ ፍጡራን ናቸው። የነቢያት ሁሉ ቁንጮና ከመልክተኞች ሁሉ አላህ ዘንድ ታላቅ ደረጃ ያላቸውን ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) እንኳ አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏቸዋል:-

﴿ قل لا أملك لنفسي نفعا ولا ضرا إلا ما شاء الله، ولو كنت أعلم الغيب لاستكثرت من الخير وما مسني السوء، ان أنا الا نذير وبشير لقوم يؤمنون ﴾ الأعراف:١٨٨
﴿ قل انى لا أملك لكم ضرا ولا رشدا، قل انى لن يجيرنى من الله أحد، ولن أجد من دونه ملتحدا ﴾ الجن:٢١ - ٢٢

« አላህ የሻውን በስተቀር ለራሴ ጥቅምንም ፡ ጉዳትንም፡ አልችልም፡ ሩቅንም (ምስጢር) የማውቅ በነበርኩ ኖሮ ከመልካም ነገር ባበዛሁና ክፉም ነገር ባልነካኝ

58 አል-ነሕል /16/: 36
59 ፋጢር /35/: 24
60 አል-ማኢዳ /5/:44

ነበር፤ እኔ ለሚያምኑ ሕዝቦች አበሣሪና አስፈራሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው።»[61]

« እኔ ለናንተ ጉዳትንም ቀጥታንም አልችልም በላቸው። እኔ ከአላህ ቅጣት አንድም አያድነኝም፤ ከርሱም ሌላ መጠጊያን አላገኝም በላቸው።»[62]

መልክተኞች እንደሌላው ሰው ሁሉ የመታመም የመሞት የመብላት የመጠጣትና ሌሎች ሁኔታዎች የሚታይባቸው ፍጡራን ናቸው። አላህ (ሱ.ወ)ስለነቢዩ ኢብራሂም እንዲህ ብሏል:-

﴿ والذى هو يطعمنى ويسقين، وإذا مرضت فهو يشفين، والذى يميتنى ثم يحيين﴾ الشعراء:٧٩ - ٨١

« ያም እርሱ የሚያበላኝና የሚያጠጣኝ ነው። በታመምኩ ጊዜ እርሱ ያሽረኛል። ያም የሚገድለኝ፤ ከዚያም ሕያው የሚያደርገኝ ነው።»[63]

ነቢዩ መሐመድም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

( إنما أنا بشر مثلكم أنسى كما تنسون فإذا نسيت فذكرونى)

« እኔ እንደናንተው ሰው እንጂ ሌላ አይደለሁም። እናንተ እንደምትረሱ ሁሉ እኔም እረሳለሁና ስረሳ አስታውሱኝ።»

መልክተኞች አላህ ዘንድ ካላቸው ከፍተኛ ደረጃ ጋር ለአላህ ተገዥ ዎችና ቅን ታዛዦች መሆናቸውን በማሞገስ ስለነሱ ተናግሯል። ነቢዩ ኑሕን (ሰ.ዐ.ወ) እና ነቢዩ መሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) አስመልክቶ እንዲህ ብሏል:-

---

61 አል- አዕራፍ /7/:188
62 አል-ጂን/72/:21–22
63 አል-ሹዐራእ /26/: 79–81

﴿ إنه كان عبدا شكورا﴾ الاسراء:٣

﴿ تبارك الذى نزل الفرقان على عبده ليكون
للعالمين نذيرا﴾ الفرقان:١

«... እርሱ በብዙ አመስጋኝ ባሪያ ነበርና።»[64]

«ያ ፉርቃንን (እውነትን ከውሸት ለይውን መጽሐፍ ቁርአንን) በባሪያው ላይ፣ ለዓለማት አስፈራሪ ይኾን ዘንድ፣ ያወረደው (አላህ)፣ ክብሩና ጥራት ተገባው።»[65]

ስለ ነቢዮች አብራሂም፣ እስሐቅና ያዕቆብ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ واذكر عبادنا إبراهيم، واسحاق ويعقوب أولى الأيدى، والأبصار، إنا أخلصناهم بخالصة ذكرى الدار، وإنهم عندنا لمن المصطفين الأخيار﴾ ص:٤٥ - ٤٧

«ባሮቻችንንም ኢብራሂምን፣ ኢስሐቅንና ያዕቆብንም፣ የኃይልና የማስተዋል ባለ ቤቶች የኾኑትን አውሳቸው። እኛ ጥሩ በኾነች ጠባይ መረጥናቸው፤ (እርሷም) የመጨረሻይቱን አገር ማስታወስ ናት። እነርሱም እኛ ዘንድ ከመልካሞቹ ምርጦች ናቸው።»[66]

ስለነቢዩ ዒሳም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

64 አል-ኢስራእ /17/:3
65 አል- ፉርቃን/25/:1
66 ሷድ /38/: 45–47

﴿ إن هو إلا عبد أنعمنا عليه وجعلناه مثلا لبني اسرائيل﴾

الزخرف:٥٩

« እርሱ በርሱ ላይ የለገስንለት፣ ለእስራኤልም ልጆች ታምር ያደረግነው የኾነ ባሪያ እንጅ ሌላ አይደለም።» [67]

## በመልክተኞች (በሩሱል) ማመን አራት ነገሮችን ያካትታል

አንደኛ– ከአላህ በትክክል የተላኩ መሆናቸውን ማመን፤ ከመልክተኞች ውስጥ ያንዱንም መልክት ያስተባበለ ሰው በሁሉም የአላህ ነቢያትና መልክተኞች እንዳላመነ ይቆጠራል። አላህ (ሱ.ወ) ስለነቢዩ ኑሕ (ሰ.ዐ.ወ) ሕዝብ ሲናገር እንዲህ ብሏል:-

﴿ كذبت قوم نوح المرسلين﴾ الشعراء: ١٠٤

« የኑሕ ሕዝቦች መልክተኞችን አስተባበሉ።» [68]

የኑሕ ሕዝቦች በወቅቱ ያስተባበሉት መልክተኛውን ኑሕን ብቻ ቢሆንም አንዱን መልክተኛ ማስተባበል ማለት ከአላህ የተላኩ መልክተኞችን በጥቅሉ እንደማስተባበል ስለሚቆጠር አላህ (ሱ.ወ) ሕዝቦቹ ኑሕን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም እንዳስተባበሉ ለማመልከት «መልክተኞችን አስተባበሉ» ብሏል። በዚህ መሠረትም ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ያስተባበሉና ያልተከተሏቸው ክርስትያኖች ሙሐመድን ብቻ ሳይሆን ነቢዩ ዒሳንም (ሰ.ዐ.ወ) ያስተባበሉና ያልተከተሏቸው ናቸው ማለት ነው። በተለይ ደግሞ ነቢዩ ዒሳ

---

67 አል- ዙኽሩፍ /43/: 59
68 አሽ- ሹዐራእ /26/: 104

ነቢዩ ሙሐመድ ከርሳቸው ዘመን በኋላ እንደሚመጡ ተከታዮቻቸውን አብስረው ነበር። ይህ ብስራት ከጥመት መንገድ የሚያድናቸውና ወደ ቀጥተኛው የአላህ ጎዳና የሚመራቸው የአላህ መልክተኛ ይመጣላችኋል ከማለት ውጭ ሌላ ትርጉም ሊኖረው አይችልም።

ሁለተኛ– በስማቸው በተለይ ባወቅናቸው እንደ ሙሐመድ፣ ኢብራሂም ሙሣ፣ ዒሳና ኑሕ (ሰ.ዐ.ወ) ባሉት ማመን፤

እነዚህ አምስቱ « ኡሉል ዐዝም» ወይም ጽኑና ቆራጦቹ በመባል የሚታወቁ ሲሆን አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ በተምረት ሁለት ቦታ ላይ አውስቷቸዋል:-

﴿ وإذ أخذنا من النبيين ميثاقهم ومنك ومن نوح، وإبراهيم، وموسى، وعيسى ابن مريم﴾ الأحزاب:٧

﴿شرع لكم من الدين ما وصى به نوحا والذى أوحينا إليك وما وصينا به إبراهيم، وموسى، وعيسى، أن أقيموا الدين ولاتتفرقوا فيه﴾ الشورى:١٣

« ከነቢዮችም የጠበቅ ኪዳናቸውን፤ ከአንተም፤ ከኑሕም፤ ከኢብራሂምም፤ ከሙሳም፤ ከመርየም ልጅ ዒሳም፤ በያዝን ጊዜ (አስታውስ)፤ ... »[69]

« ለናንተም ከሃይማኖት ያንን በርሱ ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ፤ ያንንም ወደአንተ ያወረድነውን፤ ያንንም በርሱ ኢብራሂምን፤ ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን፤ ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ፤ በርሱም አትለያዩ፤ ማለትን (ደነገገ)፤ ... »[70]

ስማቸውን የማናውቃቸውን ነቢያት በተመለከተ ግን በአጠቃላይ እናምንባቸዋለን። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

---

69 አል– አሕዛብ /33/: 7
70 አል– ሹራ /42/:13

﴿ ولقد أرسلنا من قبلك منهم من قصصنا عليك ومنهم من لم نقصص عليك﴾ عامر:٧٨

« ካንተ በፊትም መልክተኞችን በእርግጥ ልከናል፤ ከነሱ ባንተ ላይ የተረክንልህ አለ፤ ከነሱም ባንተ ላይ ያልተረክነው አለ። ... »[71]

ሦስተኛ– ስለነሱ የተላለፈውንና ትክክለኛ የሆነውን ታሪክ አምና መቀበል፤ አራተኛ– ከነርሱ መካከል ወደኛ በተላኩት– በማጠቃለያቸው በሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መላው የሰው ልጅ የተላኩ መልክተኛ መሆናቸውን አምና በመቀበል ሕጋቸውን (ሸሪዓን) ተግባራዊ ማድረግ፤ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ فلا وربك لا يؤمنون حتى يحكموك فيما شجر بينهم، ثم لا يجدوا في أنفسهم حرجا مما قضيت ويسلموا تسليما﴾ النساء:٦٥

« በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስኪያስፈርዱህ፤ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስኪያገኙና ፍጹም መታዘዝን እስኪታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይኾኑም)።»[72]

በመልክተኞች ማመን ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች:-

አንደኛ– አላህ (ሱ.ወ) ለባሮቹ ምን ያህል ርህሩህ እንደሆነ ያሳውቃል። ወደ ቀጥተኛ ጉዳናው ሊመሩዋቸውና እርሱን እንዴት እንደሚገዙት ያብራሩላቸው ዘንድ አላህ (ሱ.ወ) ወደ ሰው ልጆች መልክተኞችን መላኩ

---

71 አል– ሙእሚን /40/: 78
72 አል– ኒሳእ /4/: 65

ለሰው ልጆች የለገሰውን ጸጋና እንክብካቤ ያመላክታል። የሰው ልጅ አእምር እነዚህን መለኮታዊ ሕግጋት በገዛ ራሱ ሊያውቅ አይችልምና።

ሁለተኛ– ለዚህ ታላቅ ጸጋ አላህን (ሱ.ወ) ማመስገን፣

ሦስተኛ– መልክተኞችን መውደድ፡ ነገር፡ የአላህ (ሱ.ወ) መልእክተኞች ስለሆኑ፡ አላህን በፍጹምነት ስለሚገዙት የተጣለባቸውን ኃላፊነት ተወጥተው የአላህን መልክት በታማኝነት ስላደረሱና ባርቹን በቅንነት ስለመከሩ ተገቢያቸው በሆነ መንገድ መልክተኞቹን ማወደስ።

አላህ (ሱ.ወ) ከሰዎች መካከል መልክተኞችን አይልክም፣ ሰብዓዊ ፍጡራን የአላህ መልክተኛ መሆን አይችሉም በሚል፡ ዕብሪተኞች መልክተኞችን አስተባብለዋል። አላህ (ሱ.ወ) ይህን መሠረት የለሽ አባባል በማስተባበል እንዲህ ብሏል:-

﴿ وما منع الناس أن يؤمنوا إذ جاء هم الهدى إلا أن قالوا أبعث الله بشرا رسولا، قل لو كان فى الأرض ملائكة يمشون مطمئنين، لنزلنا عليهم من السماء ملكا رسولا﴾ الاسراء:٩٥

« ሰዎችንም፡ መሪ (ቁርአን) በመጣላቸው ጊዜ ከማመን፡ አላህ ሰውን መልክተኛ አድርጎ ላከን? ማለታቸው እንጂ ሌላ አልከለከላቸውም። በምድር ላይ ረግተው የሚኼዱ መላእክት በነበሩ ኖሮ፡ በነሱ ላይ (ከጎሳቸው) የመልአክን መልክተኛ ባወረድን ነበር፡ በላቸው።» [73]


ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ ሰዎች ወደሚኖሩባት መሬት የሚላክ መልክተኛ እንደነሱው ያለ የሰው ልጅ ወገን መሆን አለበት፤ የምድር ነዋሪዎች መላእክት ቢሆኑ ኖሮ አላህ ከሰማይ መልአክን መልክተኛ አድርጎ በላከላቸው ነበር በማለት አላህ (ሱ.ወ) አባባላቸውን ውድቅ አድርጓል።

73 አል- ኢስራእ /17/ 94-95

በተመሳሳይ ሁኔታም መልክተኞችን ያስተባበሉ ወገኖች የተናገሩትን እንደ ሚከተለው ገልጿል:-

﴿ إن أنتم إلا بشر مثلنا تريدون أن تصدونا عما كان يعبد اباؤنا، فأتونا بسلطان بين، قالت لهم رسلهم: إن نحن إلا بشر مثلكم ولكن الله يمن على من يشاء من عباده، وما كان لنا أن نأتيكم بسلطان إلا بإذن الله ﴾ إبراهيم: ١٠ ١١

« ... (ሕዝቦቹም) ፡- እናንተ ብጤያችን ሰው እንጂ ሌላ አይደላችሁም፤ አባቶቻችን ይገዙት ከነበሩት ልትከለክሉን ትሻላችሁ፤ ግልጽንም አስረጅ (ከመጣችሁት ሌላ) አምጡልን አሉ። መልክተኞቻቸውም ለነርሱ አሉ:- እኛ ብጤያችሁ ሰው እንጂ ሌላ አይደለንም፤ ግን አላህ ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ ይለግሳል፤ ለኛም በአላህ ፈቃድ እንጂ ማስረጃን ልናመጣላችሁ አይገባንም፤ ...»[74]



74 ኢብራሂም /14/: 10–11

## በመጨረሻው ቀን ማመን

የመጨረሻው ቀን ማለት ሰዎች ከሞት ተቀስቅሰው ለምርመራና እንደየሥራቸው ተገቢ ምንዳቸውን ለመቀበል የሚነሱበት የትንሣኤ ቀን ነው። የመጨረሻ ቀን የተባለበት ምክንያት ገነት የሚገቡትም ሆኑ ገሀነም የሚገቡት ሁሉም በየቤቱ ስለሚገባ ከዚያ ቀን በኋላ ሌላ ቀን ስለሌለ ነው።

## በመጨረሻው ቀን ማመን ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል

<u>አንደኛ</u>– ከሞቱ በኋላ ዳግም መቀስቀስ (በዕስ) መኖሩን ማመን፤ ይህ ማለት ሁለተኛው መለከት ሲነፋ ሙታን በሙሉ ራቁታቸውን ያለምንም ልብስ፣ ያለ ጫማ ባዶ እግራቸውን ያልተገረዙ ሆነው የዓለማት ፈጣሪ ጌታ ፊት ለፍርድ ለመቅረብ በሚቀሰቀሱበት ቀን ማመን ማለት ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ كما بدأنا أول خلق نعيده وعدا علينا إنا كنا فاعلين﴾

الأنبياء:١٠٤

« ... የመጀመሪያን ፍጥረት እንደ ጀመርን፣ እንመልሰዋለን፣ (መፈጸም) በኛ ላይ የኾነን ቀጠሮ ቀጠርን፣ (የቀጠርነውን) ሠሪዎች ነንና።»[75]

ከሞት መቀስቀስ ቁርአን ሱንና እና የሙስሊሞች የጋራ አቋም (ኢጅማዕ) ያረጋገጡት ፍጹማዊ እውነት ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ثم إنكم بعد ذلك لميتون، ثم إنكم يوم القيامة تبعثون﴾ المؤمنون :١٥ - ١٦

« ከዚያም እናንተ ከዚህ በኋላ በእርግጥ ሟቾች ናችሁ። ከዚያም እናንተ በትንሣኤ ቀን ትቀሰቀሳላችሁ።»[76]

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

(يحشر الناس يوم القيامة حفاة غرلا) متفق عليه

« ሰዎች በትንሣኤ ቀን ባዶ እግራቸውን ያልተገረዙ ሆነው ከሞት ይቀሰቀሳሉ።»[77]

---

75 አል- አንቢያ /21/: 104
76 አል- ሙእሚኑን /23/: 15–16
77 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

የሙስሊሞች የጋራ አቋምም ይህንኑ ያረጋግጣል። ይህ ፍጥረት መጨረሻ ኖርት ሁሉም ነገ ከጠፋ በኋላ ሰዎች ሁሉ የየሥራቸውን ዋጋ ቀደም ሲል አላህ በላካቸው ነቢያት አማካይነት የተላለፈላቸውን መለኮታዊ ሕግ በመተግበር ረገድ ባደረጉት ጥረት ላይ የተመረኮዘ ምንዳ ወይም ቅጣት የሚገኙበት ማግኘት እንዳለባቸው የአላህ (ሱ.ወ) ጥበብ የሚወስነው ጉዳይ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ أفحسبتم أنما خلقناكم عبثا، وأنكم إلينا لاترجعون﴾

المؤمنون:١١٥

« የፈጠርናችሁ፣ ለከንቱ መኾኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መኾናችሁን ጠረጠራችሁንን » [78]

አላህ (ሱ.ወ) ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ إن الذى فرض عليك القرآن لرادك الى معاد﴾

القصص:٨٥

« ያ ቁርአንን የተከፋፈለ ኾኖ ባንተ ላይ ያወረደው (አምላክ)፣ ወደ መመለሻ በእርግጥ መላሺህ ነው፣ ...» [79]

<u>ሁለተኛ</u> – ምርመራ መኖሩንና ለሁሉም እንደየሥራው ዋጋ የሚሰጠው መሆኑን ማመን፤ አንድ ሰው በመጀመሪያ ምድራዊ ሕይወቱ በፈጸማቸው ሥራዎች ሁሉ ላይ ምርመራ ይደረግበትና መልካም ሥርቶ ከሆነ ገነት መጥፎ ሥርቶ ከሆነም የከፋ የገሐነም እሳት ይገባል። ይህ እምነት በቁርአን በሱንና እና በሙስሊሞች የጋራ አቋም (እጅማዕ) የተረጋገጠ ነው።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

---

78 አል– ሙእሚኑን /23/: 115
79 አል–ቀሰስ /28/: 85 .

﴿ إن إلينا إيابهم ثم إن علينا حسابهم﴾ الغاشية: ٢٥ ٢٦

﴿ من جاء بالحسنة فله عشر امثالها، ومن جاء بالسيئة فلا يجزى إلا مثلها، وهم لايظلمون﴾ الأنعام: ١٦٠

﴿ ونضع موازين القسط ليوم القيامة، فلاتظلم نفس شيئا، وان كان مثقال حبة من خردل أتينا بها، وكفى بنا حاسبين﴾ الأنبياء: ٤٧

«መመለሻቸው ወደኛ ብቻ ነው። ከዚያም ምርመራቸው በኛ ላይ ብቻ ነው።»[80]

«በመልካም ሥራ የመጣ ሰው፡ ለርሱ ዐሥር ብጤዎቿ አሉት፤ በክፉ ሥራም የመጣ ሰው ብጤዋን እንጅ አይመነዳም፤ እነርሱም አይበደሉም።»[81]

«በትንሣኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን፡ ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም፤ (ሥራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርሷን እናመጣታለን፤ ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ።»[82]

ከእብኑ ዑመር በተላለፈው ሐዲስ ውስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

( ان الله يدنى المؤمن فيضع عليه كنفه ويستره، فيقول: أتعرف ذنب كذا؟ أتعرف ذنب كذا؟ فيقول نعم: أى رب حتى إذا قرربذنوبه، ورأى أنه قد هلك قال: قد سترتها

80 አል- ጋሺያህ /88/ 25-26
81 አል- አንዓም /6/ 160
82 አል- አንቢያ /21/ 47

عليك في الدنيا، وأنا أغفرها لك اليوم، فيعطى كتاب حسناته، وأما الكفار والمنافقون فينادى بهم على رؤس الخلائق ( هؤلاء الذين كذبوا على ربهم، ألا لعنة الله على الظالمين) متفق عليه

( أن من هم بحسنة فعملها، كتبها الله عنده عشر حسنات إلى سبعمائة ضعف إلى أضعاف كثيرة، وإن من هم بسيئة فعملها، كتبها الله سيئة واحدة)

« አላህ አማኝ የሆነ ሰውን (ሙእምንን) ያቀርብና ገበናውን በመሸፈን:- ‹እንዲህ ያለውን ኃጢአትህን እንደዚህ ያለውን ኃጢአትህን ታውቃለህን› ይለዋል። (አማኙም) አዎ ጌታዬ አውቃለሁ ይላል። ኃጢአቶቹን አምኖ ጥፋት እንደተረጋገጠበት የተረዳ መሆኑን ሲመለከትም:- ‹ በመጀመሪያ ምድራዊ ሕይወትህ ጊዜም ደብቄልሃለሁ። እነሆ ዛሬም ይቅር ብዬ አምርሃለሁ› ይለውና አማኙ የመልካም ሥራዎቹን መዝገብ ይሰጣል። ለከሐዲዎችና ለአስመሳይ መናፍቃን ግን ‹እነዚሁ ጌታቸው ላይ የቀጠፉ ናቸው› የአላህ ቁጣም በበዳዮች ላይ ይሁን› ተብሎ በተሰበሰበ ፍጡራን ፊት ይታወጃል።»[83]

« አንድ ሰው መልካም ሥራ ለመሥራት አስቦ ከሠራው አላህ ከአሥር መልካም ምንዳ ጀምሮ እስከ ሰባት መቶ እጥፍና እስከ ብዙ እጥፍ ድርብ ምንዳ ድረስ እርሱ ዘንድ ይጽፍለታል። አንድ ሰው መጥፎ ነገር አስቦ ከሠራው ግን አንድ መጥፎ ሥራ ብቻ አላህ ይመዘግብበታል።»

ምርመራ ስለመኖሩና ለሁሉም እንደ የሥራው ተገቢ ዋጋ የሚከፈለው ስለመሆኑ መስሊሞች በአንድ ድምጽ የተስማሙበት እውነታ ነው። የአላህ (ሱ.ወ) ጥበብም ይህንኑ ግዴታ ያደርጋል። አላህ (ሱ.ወ) መጻሕፍት አውርዷል። መልክተኞችን ልኳል። መልክተኞች ያስተማሩትን ነገር እንዲቀበሉና ተግባራዊ እንዲያደርጉ በሰዎች ላይ ግዴታ ጥሏል። መልክተኞቹ ያስተማሩትን የሚጻረሩ ወገኖችን መዋጋት ልጆቻቸውን ሴቶቻቸውንና ንብረታቸውን መውረስ ፈቅዷል። ምርመራ ጥያቄና ለሁሉም እንደ የሥ

83 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

ራው ምንዳ ወይም ቅጣት የመስጠት ፍትሕ የማይኖር ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ መደንገግ ከንቱ በሆነ ነበር። ጥበበኛው አምላክ አላህ (ሱ.ወ) ከዚህ ከንቱነት የጠራ ጌታ ነው። ይህን እውነታ አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ فلنسألن الذين أرسل إليهم، ولنسألن المرسلين،فلنقصن
عليهم بعلم،وما كنا غائبين﴾

الأعراف:٦ – ٧

«እነዚያንም ወደነሱ ነብያት የተላኩባቸውን (ሕዝቦች) በእርግጥ እንጠይቃቸዋለን። የተላኩትን መልክተኞችንም በእርግጥ እንጠይቃለን፤ በነርሱም ላይ (የሰበሩበትን ሁሉ) ከዕውቀት ጋር በእርግጥ እንተርክላቸዋለን፤ የራቅንም አልነበርንም።» [84]

ሦስተኛ– ገነትና እሳት (ገሐነም) መኖሩን ማመን፤

በገነትና በእሳት (ገሐነም) መኖር ማመን ማለት የፍጥረታት ሁሉ መጨረሻ ከሁለቱ በአንደኛው መሆኑን ማመን ማለት ነው። ጀነት የነዚያ አላህ እንዲያምኑ በጠየቃቸው ነገር ሁሉ ያመኑ አላህንና መልክተኛውን በቅንነት የታዘዙ ለአላህ ፍጹም በመሆን መልክተኞቹን ለተከተሉ ፈሪሀ አላህ የሆኑ ምዕመናን አገር ነች። ገነት ታይተውና ተሰምተው የማይታወቁ፣ በሰው አእምሮ ታስበው የማይታወቁ የመደሰቻ ዓይነቶች የተትረፈረፉባት መኖሪያ አገር ነች። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ إن الذين ءامنوا وعملوا الصالحات، أولئك هم خير البرية،
جزاؤهم عند ربهم جنات عدن تجرى من تحتها الأنهار، خالدين
فيها أبدا، رضي الله عنهم ورضوا عنه، ذلك لمن خشي ربه﴾

البينة:٧ – ٨

84 አል– አዕራፍ /7/: 6–7

﴿ فلا تعلم نفس ما أخفي لهم من قرة أعين جزاء بما كانوا يعملون﴾ السجدة:١٧

« እነዚያ ያመኑትና መልካሞችንም የሠሩት፣ እነዚያ እነሱ ከፍጥረት ሁሉ በላጭ ናቸው። በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው የመኖሪያ ገነቶች ናቸው፤ በውስጣቸው ለዘላለም ዘውታሪዎች ሲኾኑ፡ (ይገዙባቸዋል)። አላህ ከነሱ ወደደ ፤ ከርሱም ወደዱ፤ ይህ ጌታውን ለፈራ ሰው ነው።»[85]

« ያሠሩትም በነበሩት ለመመንዳት፣ ከዓይኖች መርጊያ ለነሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ)፡ ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም።»[86]

እሳት (ገሐነም) ደግሞ እርሱን ባስተባበሉና መልክተኞቹ ላይ ባመጹ ከሐዲዎችና በዳዮች አላህ (ሱ.ወ) ያዘጋጀላቸው የሥቃይ ሥፍራ ነች። ይህ ነው ተብሎ የማይታሰብ የሥቃይና የውርደት ዓይነቶች ያጠቃለለች የመቀጣጫ ቦታ ነች። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ واتقوا النار التى أعدت للكافرين﴾ آل عمران:١٣١

﴿ إنا أعتدنا للكافرين نارا أحاط بهم سرادقها، وان يستغيثوا يغاثوا بماء كالمهل يشوى الوجوه، بئس الشراب وساءت مرتفقا﴾ الكهف:٢٩

﴿ إن الله لعن الكافرين، وأعد لهم سعيرا، خالدين فيها أبدا، لا يجدون وليا ولا نصيرا، يوم تقلب وجوههم فى النار، يقولون يا ليتنا أطعنا الله وأطعنا الرسولا﴾ الأحزاب،٦٤ - ٦٦

85 አል- በይናህ /98/:7-8
86 አል- ሰጅዳህ /32/: 17

« ያችንም ለከሐዲዎች የተደገሰችውን እሳት ተጠንቀቁ።» [87]

« ... እኛ ለበደለኞች አጥሯቸው በነሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል፡ (ከጥም) እርዳታንም ቢፈልጉ፡ እንደዘይት ዝቃጭ ባለ ፡ ፊቶችን በሚጠብስ ውሃ፡ ይረዳሉ፡ መጠጡ ከፋ! መደገፊያይቱም ምንኛ አስከፋች! » [88]

« አላህ ከሐዲዎችን በእርግጥ ረግሟቸዋል፡ ለነርሱም የተጋጋመችን እሳት አዘጋጅቷል። በርሷ ውስጥ ዘለዓለም ዘውታሪዎች ሲኾኑ፡ ወዳጅም ረዳትም አያገኙም። ፊቶቻቸው በእሳት ውስጥ በሚገለባበጡ ቀን፡ ዋ ምኞታችን! አላህን በተገዛን፡ መልክተኛውንም በታዘዝን ኖሮ እያሉ ይጸጸታሉ።»[89]

ከሞት በኋላ በሚሆን መቃብር ውስጥ በሚኖረው ሥቃይ ፈተናና ደስታ በመሳሰሉት ነገሮች ማመን በመጨረሻው ቀን በማመን ሥር ይጠቃለላል።

ሀ– የመቃብር ውስጥ ፈተና፡- ይህ ፈተና ሟቹ ከተቀበረ በኋላ ጌታው ማን እንደሆን፡ ሃይማኖቱ ምን እንደሆነና ነቢዩ ማን እንደሆን የሚጠየቅበት ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ወቅት በጽናው የአላህ ቃል ላመኑ ምዕመናን አላህ (ሱ.ወ) ጽናት ይሰጥና– ጌታዬ አላህ ነው፡ ሃይማኖቴ እስላም ነው፡ ነቢዩም ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው በማለት ይመልሳሉ። አላህ በዳዮችን ያጠምና ከሐዲዎች ሃ! ሃ! አላውቅም ብለው ይመልሳሉ። አስመሳይ መናፈቁ ወይም ተጠራጣሪው ደግሞ፡ አላውቅም ሰዎች ሲሉ ሰምቼ ነው ያልኩት ብሎ ይመልሳል።

ለ– መቃብር ውስጥ ያለው ሥቃይና ደስታ፡- የመቃብር ውስጥ ሥቃይን በተመለከተ በዳዮች መናፍቃንና ከሐዲዎች መቃብራቸው ውስጥ ይሠቃያሉ። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

---

87 አል–ኢምራን /3/: 131
88 አል–ከህፍ /18/: 29
89 አል– አሕዛብ /33/: 64–66

﴿ ولو ترى إذ الظالمون فى غمرات الموت، والملائكة باسطوا أيديهم، أخرجوا أنفسكم، اليوم تجزون عذاب الهون بما كنتم تقولون على الله غير الحق وكنتم عن آياته تستكبرون﴾

الأنعام:٩٣

« ... በደለኞችንም በሞት መከራዎች ውስጥ በኾኑ ጊዜ መላእክት እጆቻቸውን ዘርጊዎች ኾነው (ለቅጣት) ነፍሶቻችሁን አውጡ፤ በአላህ ላይ እውነት ያልሆነን ነገር ትናገሩ በነበራችሁትና ከአንቀጾቹም ትኮሩ በነበራችሁት ምክንያት፣ ዛሬ የውርደትን ቅጣት ትመነዳላችሁ፣ (የሚሏቸው ሲኾኑ) ብታይ ኖሮ፣ ( አስደናቂን ነገር ባየህ ነበር)።»[90]

﴿ النار يعرضون عليها غدوا وعشيا، ويوم تقوم الساعة أدخلوا آل فرعون أشد العذاب﴾ غافر:٤٦

« እሳት በጧትና በማታ በርሷ ላይ ይቀረባሉ፤ ሰዓቲቱም በምትኾንበት ቀን የፈርዖንን ቤተሰቦች ብርቱን ቅጣት (ገሀነምን) አግቡዋቸው (ይባላል)።»[91]

ሙስሊም ዘይድ ብን ሳቢትን በመጥቀስ በዘገቡት ሐዲስ ውስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

( فلولا أن لا تدافنوا لدعوت الله أن يسمعكم من عذاب القبر الذى أسمع منه، ثم أقبل بوجهه فقال: تعوذوا بالله من عذاب النار قالوا: نعوذ بالله من عذاب النار. فقال: تعوذوا من عذاب القبر، قالوا: نعوذ بالله من عذاب القبر، قال: تعوذوا من الفتن ما

90 አል- አንዓም /6/: 93
91 አል- ሙእሚን /40/: 46

ظهر منها وما بطن، قالوا: نعوذ بالله من الفتن ما ظهر منها وما بطن، قال: تعوذوا بالله من فتنة الدجال قالوا: نعوذ بالله من فتنة الدجال) رواه مسلم

« ... (ድምጹን በመስማታችሁ ምክንያት ፈላችሁን)) መቃብር ትተዋላችሁ ብዬ ባልሰጋ ኖሮ እኔ እየሰማሁ ያለሁትን (የመቃብሩ ሰዎች ያሉበትን) የመቃብር ስቃይ አላህ እንዲያሰማችሁ በለመንኩ ነበር።» አሉና ፊታቸውን ወደ ሰሐቦች በማዞር:- ‹ከእሳት ቅጣት በአላህ ተጠበቁን በሉ› አሏቸው። እነሱም አላህ ሆይ! ከእሳት ቅጣት በአንተ እንጠበቃለን አሉ። ‹ከመቃብር ቅጣት በአላህ ተጠበቁ› አሏቸው። ከመቃብር ቅጣት በአላህ እንጠበቃለን አሉ። ‹ከፈተናዎች ከግልጹም ከስውሩም በአላህ ተጠበቁን በሉ› አሏቸው። ከፈተናዎች ከግልጹም ከስውሩም በአላህ እንጠበቃለን አሉ። ‹ከደጅ–ጃል ፈተና በአላህ ተጠበቁን በሉ› አሏቸው። ከደጅ–ጃል ፈተና በአላህ እንጠበቃለን አሉ።» [92]

የመቃብር ውስጥ ደስታ ግን ለእውነተኞቹ ምዕመናን ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ إن الذين قالوا ربنا الله تتنزل عليهم الملائكة أن لا تخافوا ولاتحزنوا، وأبشروا بالجنة التى كنتم توعدون﴾

فصلت: ٣٠

﴿ فلولا إذا بلغت الحلقوم، وأنتم حينئذ تنظرون، ونحن أقرب إليه منكم ولكن لاتبصرون، فلولا ان كنتم غير مدينين، ترجعونها ان كنتم صادقين، فأما إن كان من المقربين فروح وريحان وجنة نعيم..﴾ الواقعة: ٨٣ - ٨٩٠

92 ሙስሊም የዘገበው ሐዲስ

« እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉ፣ ከዚያም ቀጥ ያሉ፣ አትፍሩ፣ አትዘኑም፣ በዚያችም ተስፋ ቃል ትደረግላችሁ በነበረችሁት ገነት ተበሰሩ፣ በማለት በነሱ ላይ መላእክት ይወርዳሉ።»[93]

« (ነፍስ) ጉሮሮንም በደረሰች ጊዜ እናንተ ያን ጊዜ የምታዩ ስትኾኑ። እኛም፣ ግን አታዩም እንጅ ከናንተ ይልቅ ወደርሱ የተቀረብን ስንኾን። የማትገዙም ከኾናችሁ። እውነተኞች እንደኾናችሁ፣ (ነፍሲቱን ወደ አካሉ) ለምን አትመልሷትም። (ሟቹ) ከባለሟሎቹ ቢኾንማ። (ለርሱ) ዕረፍት፣ መልካም ሲሳይም፣ የመጠቀሚያ ገነትም አለለው።»[94]

አንድ አማኝ (ሙእሚን) ለሁለቱ መላእክት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ የሚሆነውን ሁኔታ አስመልክተው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

( ينادى مناد من السماء أن صـدق عبدى، فأفرشـو ه مـن الجنـة، وألبسوه من الجنة، وافتحـوا لـه بابـا إلـى الجنـة، قـال فيأتيـه مـن روحها وطيبها، ويفسح له فى قبره مد بصره) رواه أحمد

« ከሰማይ ጠሪ ይጣራና ባሪያዬ እውነት ተናግሯልና ከገነት (ምንጣፍ) አንጥፉለት፣ ከገነት (ልብስ) አልብሱት፣ ወደ ገነት የሚወስድ በርም ክፈቱለት ይላል። በዚህም (ከገነት) እርይታዋና መልካም መዓዛዋ ይመጡለታል፣ የዓይኑ እይታ እስከ ሚደርስበት ርቀት ድረስም መቃብሩ ይሰፋለታል።»[95]

በመጨረሻው ቀን ማመን ከሚያስገኛቸው ከፍተኛ ውጤቶች መካከል:-

<u>አንደኛ</u>:- ለዚያ ቀን ምንዳ ተስፋ በማድረግ ለመልካም ሥራ መጓጓትና ፍላጐት ማሳደጉ፤

93 ሓሚም አስሰጅዳህ /41/:30
94 አል- ዋቂዓህ /56/: 83-89
95 አሕመድ የዘገቡት ሐዲስ

ሁለተኛ:- የአላህን ትዕዛዝ መጣስ በዚያ ቀን የሚያስከትለውን መሪር ቅጣት በማሰብ ከከፉ ሥራ የመቆጠብ ግፊት ማሳደግ፣

ሦስተኛ:- አንድ አማኝ (ሙእሚን) በዚህች ጠፊ ዓለም ከሚያመልጡት ነገሮች በወዲያኛው ዓለም በሚኖረው ተድላና ምንዳ መጽናናቱ፣ ይገኙበታል።

ከሓዲዎች ከሞት በኋላ ዳግም መቀስቀስ የማይቻል ነው በማለት አስተባብለዋል። ይህ አባባል ግን ሸሪዓው ተጨባጩ ሁኔታና አእምሮ በማስረጃ የሚያስባብሉት ውሸት ነው።

የሸሪዓን ማስረጃ በተመለከተ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ زعم الذين كفروا ان لن يبعثوا قل بلى وربى لتبعثن، ثم لتنبؤن بما عملتم، وذلك على الله يسير﴾ التغابن:٧

« እነዚያ የካዱት በፍጹም የማይቀሰቀሱ መኾናቸውን አሰቡ፣ አይደለም በጌታዬ እምላለሁ፤ በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ፤ ከዚያም በሠራችሁት ሁሉ ትነገራላ ችሁ፤ ይህም በአላህ ላይ ቀላል ነው፤ በላቸው።»[96]

መለኮታዊ መጻሕፍትም በዚህ ነጥብ ላይ ሙሉ በሙሉ ይስማማሉ። ተጨባጭ ሁኔታን በተመለከተ ደግሞ አላህ (ሱ.ወ) በዚህች ዓለም ላይ ሰዎች ከሞቱ በኋላ ከመቃብራቸው ነፍስ ዘርተው እንዲቀሰቀሱ በማድረግ አሳይቷል። በአል–በቀራህ ምዕራፍ ውስጥ ይህንኑ የሚያረጋግጡ አምስት ምሳሌዎች ተመልክተዋል።

አንደኛው ምሳሌ:- የነቢዩ ሙሣ (ሰ.ዐ.ወ) ሕዝቦች አላህን በዓይናችን ካላየን በስተቀር አናምን ባሉ ጊዜ አላህ (ሱ.ወ) ገድሏቸው እንደገና አስነስቷቸዋል።

---

96 አል– ተጋቡን /64/: 7

ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብሏል:-

﴿وإذ قلتم يا موسى لن نؤمن لك حتى نرى الله جهرة، فأخذتكم الصاعقة، وأنتم تنظرون، ثم بعثناكم من بعد موتكم لعلكم تشكرون﴾ البقرة:٥٥ – ٥٦

« ሙሳ ሆይ! አላህን በግልፅ እስከምናይ ድረስ ላንተ በፍጹም አናምንልህም ባላችሁም ጊዜ (አስታውሱ)! እናንተም እየተመለከታችሁ መብረቅ ያዘቻችሁ! (ለሞት ምርመቻችሁ ሞቱ)። ከዚያም ታመሰግኑ ዘንድ ከሞታችሁ በኋላ አስነሳናችሁ።»[97]

ሁለተኛው ምሳሌ:- የእስራኤል ልጆች ከመካከላቸው ገዳዩ ሳይታወቅ ሞቶ የተገኘውን ሰው ታሪክ የሚመለከት ሲሆን የሟቹን ገዳይ ለማወቅ አላህ ባዘዛቸው መሠረት ላም አርደው በላሟ ከፊል አካል ሟቹን ሲመቱ ሟች ሕይወት ዘርቶ ገዳዩ ማን እንደሆነ ተናግሯል። ይህን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿وإذ قتلتم نفسا فادارأتم فيها، والله مخرج ما كنتم تكتمون، فقلنا اضربوه ببعضها كذلك يحي الله الموتى، ويريكم آياته لعلكم تعقلون﴾ البقرة:٧٢ – ٧٣

« ነፍስንም በገደላችሁና በርሷም (ገዳይ) በተከራከራችሁ ጊዜ (አስታውሱ)! አላህም ትደብቁት የነበራችሁትን ሁሉ ገላጭ ነው። (በድኑን) በከፊሏ (በላሚቱ) ምቱት አልን! (መቱትምና ተነሳ ገዳዩንም ተናገረ ሞተ)! እንደዚሁ አላህ ሙታንን ያስነሳል! ታውቁም ዘንድ ታምራቶቹን ያሳያችኋል።»[98]

---

97 አል–በቀራህ /2/: 55–56
98 አል–በቀራህ /2/: 72–73

ሦስተኛው ምሳሌ:- ሞትን ለመሸሽ በሺዎች የሚቆጠሩ ሆነው ከአገራቸው የወጡትን ሰዎች ታሪክ የተመለከተ ሲሆን እነዚህን ሰዎች አላህ ከገደላቸው በኋላ እንደገና ቀስቅሷቸዋል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ألم تر إلى الذين خرجوا من ديارهم وهم ألوف حذر الموت، فقال لهم الله موتوا، ثم أحياهم إن الله لذو فضل على الناس، ولكن أكثر الناس لا يشكرون﴾

البقرة:٢٤٣

« ወደ እነዚያ እነርሱ ብዙ ሺሕ ኾነው ሞትን ለመፍራት ከሀገሮቻቸው ወደ ወጡት ሰዎች ዕውቀትህ አልደረሰምን? አላህም ለነርሱ ሙቱ አላቸው፤ (ሞቱም)፤ ከዚያም ሕያው አደረጋቸው፤ አላህም በሰዎች ላይ ባለችሮታ ነው፤ ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያመሰግኑም።» [99]

አራተኛው ምሳሌ:- በአንዲት የወደመች ከተማ ውስጥ ሲያልፍ ይህች የጠፋች ከተማ እንዴት ዳግም መቀስቀስ ትችላለች ብሎ በግራሞት የተናገረውን ሰው ታሪክ የሚመለከት ነው። አላህ (ሱ.ወ) ይህን ሰው አንድ መቶ ዓመት ሞቶ እንዲቆይ ካደረገው በኋላ እንደገና የቀሰቀሰው መሆኑን እንደሚከተለው ተናግሯል:-

﴿أو كالذي مر على قرية وهي خاوية على عروشها قال: أنى يحيي هذه الله بعد موتها، فأماته الله مئة عام، ثم بعثه، قال: كم لبثت؟ قال: لبثت يوما أو بعض يوم،

---

99 አል-በቀራህ /2/: 243

قال: بل لبثت مئة عام فانظر إلى طعامك وشرابك لم يتسنه وانظر إلى حمارك ولنجعلك آية للناس وانظر إلى العظام، كيف ننشزها، ثم نكسوها لحما؟ فلما تبين له قال: اعلم ان الله على كل شيئ قدير﴾ البقرة:٢٥٩

« ወይም ያንን በከተማ ላይ እርሷ በጠራዎችዋ ላይ የወደቀች ስትኾን ያለፈውን ሰው ብጤ፤ (አላየህምን?)፡- ይህችን (ከተማ) ከሞተች በኋላ አላህ እንዴት ሕያው ያደርጋታል አለ፤ አላህም ገደለው፤ መቶ ዓመትን (አቆየውም)፤ ከዚያም አስነሳው:- ምን ያህል ቆየህ? አለው፤ አንድን ቀን ወይም የቀንን ከፊል ቆየሁ አለ፤ አይደለም መቶን ዓመት ቆየህ፤ ወደ ምግብህና ወደ መጠጥህም ያልተለወጠ ሲኾን፤ ተመልከት፤ ወደ አህያህም ተመልከት፤ ለሰዎችም አስረጅ እናደርግህ ዘንድ፤ (ይህንን ሠራን)፤ ወደ ዐጥንቶችም እንዴት እንደምናስነሳት ከዚያም ሥጋን እንደምናለብሳት ተመልከት፤ አለው፤ ለርሱም (በግልጽ) በተገለፀለት ጊዜ:- አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መኾኑን ዐውቃለሁ፤ አለ።» [100]

<u>ስምንተኛው ምሳሌ</u>:- ተወዳጁ ነቢዩ ኢብራሂም (ሰ.ዐ.ወ) ፤ አላህ (ሱ.ወ) ሙታንን እንዴት እንደገና እንደሚያስነሳ እንዲያሳያቸው የለመኑ በትን ሁኔታ የሚመለከት ታሪክ ነው። በዚህ መሠረትም አላህ (ሱ.ወ) አራት ወፎችን አርደው በመበለት በአካባቢያቸው በነበሩት ተራሮች ላይ የወፎቹን ሥጋ እንዲያስቀምጡ ኢብራሂምን አዘዛቸው። ኢብራሂም የታዘዙትን ከፈጸሙ በኋላ ወፎቹን ሲጣሩ በተራሮች ላይ የተበታተኑ አካሉ ቻቸው እየተገጣጠሙ ወደ ኢብራሂም እየሮጡ መጡ።

ይህንኑ አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وإذ قال إبراهيم رب أرني كيف تحيي الموتى؟ قال: أولم تؤمن! قال: بلى، ولكن ليطمئن قلبي. قال: فخذ

100 አል- በቀራህ/2/: 259

أربعة من الطير فصرهن إليك، ثم اجعل على كل جبل منهن جزءا ثم ادعهن يأتينك سعيا، واعلم ان الله عزيز حكيم﴾ البقرة:٢٦٠

« ኢብራሂምም ጌታዬ ሆይ! ሙታንን እንዴት ሕያው እንደምታደርግ አሳየኝ ባለ ጊዜ፣ (አላህ):- አላመንክምን? አለው፤ አይደለም (አምኛለሁ) ፤ ግን ልቤ እንዲረጋ ነው አለ፤ (አላህም):- ከበራሪዎች (ከወፎች) አራትን ያዝ፤ ወደ አንተም ሰብስባቸው፤ (ቆራርጣቸውም)፤ ከዚያም በየኮረብታው ሁሉ ላይ ከነርሱ ቁራጭን አድርግ፤ ከዚያም ጥራቸው፤ ፈጥነው ይመጡሃልና፤ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ መሆኑን ዕወቅ አለው፡፡» [101]

እነዚህ ሙታንን እንደገና ወደ ሕይወት መመለስ የሚቻል መሆኑን በተጨባጭ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ቀደም ሲል ለመርየም ልጅ ለዒሳ ሙታንን በአላህ (ሱ.ወ) ፈቃድ ከመቃብር በማስነሳት የሰጠውን ተአምራት አውስተናል፡፡

## ሕሊናዊ ማስረጃው ደግሞ በሁለት ይከፈላል

<u>አንደኛ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) ሰማያትንና መሬትን በውስጣቸው ያሉትን ፍጥረታት በአጠቃላይ ከመጀመሪያው የፈጠረ አምላክ ነው፡፡ ፍጥረታትን መጀመሪያ ማስገኘት የቻለ ፈጣሪ እንደገና ከጠፉ በኋላ መልሶ ማስገኘት አይሳነውም፡፡ ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿وهو الذى يبدأ الخلق ثم يعيده، وهو أهون عليه﴾ الروم:٢٧

101 አል– በቀራህ /2/: 260

﴿ كما بدأنا أول خلق نعيده، وعدا علينا، إنا كنا فاعلين﴾ الأنبياء:١٠٤

« እርሱም፣ ያ መፍጠርን የሚጀምር፣ ከዚያም የሚመልሰው ነው፣ እርሱም (መመለሱ) በእርሱ ላይ በጣም ገር ነው፣ ...» [102]

« ... የመጀመሪያን ፍጥረት እንደ ጀመርን፣ እንመልሰዋለን፣ (መፈጸሙ) በኛ ላይ የሆነን ቀጠሮ ቀጠርን፣ እኛ (የቀጠርነውን) ሠሪዎች ነን።» [103]

አጥንቶች በስብሰው ትቢያ ከሆኑ በኋላ እንዴት ተመልሰው ሕይወት ሊዘሩ ይችላሉ ብለው ለሚጠይቁ ወገኖች የሚከተለው መልስ እንዲሰጣቸው ሲያዝ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ قل يحييها الذي أنشأها أول مرة، وهو بكل خلق عليم﴾ يس:٧٩

« ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንት) ያስገኛት ሕያው ያደርጋታል፣ እርሱም በፍጡሩ ሁሉ (ችሎታ) ዐዋቂ ነው፣ በላቸው።» [104]

<u>ሁለተኛ</u>:- ምንም ዓይነት ዕጽዋት የሌለበት ምድረበዳ መሬት ላይ ዝናም ዘንቦ ከሁሉም ጎኑ አረንጓዴ ተክል የለመለመበት ሕያው መሬት ይሆናል። ይህን ሕይወት አልባ ደረቅ መሬት ሕያውና ለም መሬት ማድረግ የሚችል አምላክ ሙታንን እንደገና ለመቀስቀስ ቻይ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ومن آياته أنك ترى الأرض خاشعة، فإذا أنزلنا عليها الماء اهتزت، وربت، إن الذي أحياها لمحيي الموتى، إنه على كل شيئ قدير﴾ فصلت:٣٩

---

102 አል-ሩም /30/: 27
103 አል-አንቢያ /21/: 104
104 ያሲን /36/: 79

﴿ ونزلنا من السماء ماء مباركا، فأنبتنا به جنات وحب الحصيد، والنخل باسقات لها طلع نضيد، رزقا للعباد، وأحيينا به بلدة ميتا كذلك الخروج.﴾ ق: ٩ - ١١

« አንተ ምድርን ደረቅ ኾና ማየትህም ከምልክቶቹ ነው፤ በርሷም ላይ ውሃን ባወረድን ጊዜ፤ (በቡቃያዎችዋ) ትላወሳለች፤ ትነፋለችም፤ ያ ሕያው ያደረጋት ጌታ በእርግጥ ሙታንን ሕያው አድራጊ ነው፤ እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና። »[105]

« ከሰማይም ብሩክን ውሃ አወረድን፤ በርሱም አትክልቶችንና የሚታጨድን (አዝመራ) ፍሬ አበቀልን። ዘምባባንም ረዣዥም፤ ለርሷ የተደራረበ እንበጥ ያላት ስትኾን (አበቀልን)። ለባሮቼ ሲሳይ ትኾን ዘንድ (አዘጋጀናት)፤ በርሱም የሞተችን አገር ሕያው አደረግንበት፤ (ከመቃብር) መውጣትም እንደዚሁ ነው። »[106]

ከሐቅ ጉዳና ከተዛነፉ ሰዎች መካከል ከፊሉ የመቃብር ውስጥ ሲታይንና ተድላውንም በማስተባበል ከተለመደው ሕግ ውጭ የሆነ ሊሆን የማይችል ነው፣ አንዱ መቃብር ቢከፈት እንደነበረ ሆኖ እናገኘዋለን እንጂ ስፋትም ይሁን ጥበት ጨምር እናገኘውም በሚል አባባል ጠመሙ።

ይህን አባባል ሸሪዓው ነብራዊው ሁኔታና ሕሊናዊ ማስረጃ የሚያስተባብሉት ቅጥፈት ነው።

የሸሪዓውን ማስረጃ በተመለከተ የመቃብር ውስጥ ሥቃይና ደስታ ስለመኖራቸው በመጨረሻው ቀን ከማመን ሥር በሚጠቃለሉ ጉዳዮች ውስጥ በ«ለ» ውስጥ ቁርአናዊ አንቀጾችና ነቢያዊ ሐዲሶች ማስፈራችን ይታወሳል። በተጨማሪም የሚከተለውን ነቢያዊ ሐዲስ እናገኛለን:-

105 ሐ.ሚም አስሰጅዳ /41/: 39
106 ቃፍ /50/: 9–11

( خرج النبي صلى الله عليه وسلم من بعض حيطان المدينة، فسمع صوت انسانين يعذبان فى قبورهما.. أن أحدهما كان لا يستتر من البول ((وفى رواية من بوله)) وأن الآخر كان يمشى بالنميمة) رواه البخارى

« ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከመዲና አጥሮች ወጥተው ሁለት ሰዎች መቃብር ውስጥ ሲሰቃዩ ድምፃቸውን ሰሙ። ... አንደኛቸው ከሽንቱ የማይጠበቅ ነበር፤ ሌላኛው ደግሞ አሳባቂ (ሰውን የሚያጣላ ነገር አመላላሽ) ነበር።»[107]

ተጨባጩን ሁኔታ በተመለከቱ ደግሞ አንድ ሰው ተኝቶ በሕልሙ በጣም ሰፊ በሆነ ቦታ ላይ ሆኖ ሲደሰትና ሲዝናና ሊያይ ይችላል። ወይም ጠባብ አስጨናቂና ሥቃይ በመላበት ቦታ ውስጥ ሲሰቃይ ሊያይ ይችላል። ምናልባትም አንዳንድ ጊዜ በሕልሙ ምክንያት ከእንቅልፉ የሚነቃበት ሁኔታም ይኖራል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን መኝታው ላይ እንደነበረ አቤቱ ውስጥ እንዳለ መሆኑ ይታወቃል። ሞትም የእንቅልፍ ወንድም ነው። አላህ (ሱ.ወ) ለዚህ ነው እንዲህ ያለው:-

﴿ الله يتوفى الأنفس حين موتها، والتى لم تمت فى منامها فيمسك التى قضى عليها الموت ويرسل الأخرى إلى أجل مسمى﴾ الزمر:٤٢

« አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ፣ ይወስዳል፣ ያችንም ያልሞተችውን በእንቅልፏ ጊዜ፣ (ይወስዳታል)፤ ታዲያ ያችን ሞትን የፈረደባትን ይይዛታል፤ ሌላይቱንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቃታል፤... »[108]

---

107 ቡኻሪ የዘገቡት ሐዲስ

ሕሊናዊ ማስረጃን በተመለከተ ደግሞ አንድ ሰው ተኝቶ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ሙሉ በሙሉ የተጣጣመ እውነተኛ ሕልም ያያል። ምናልባትም ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) እንዳሉ በዚህች ዓለማዊ ሕይወት በነበሩበት ጊዜ በነበራቸው አኳኋን ሆነው ያያቸዋል። ነቢዩን በዚህ ሁኔታ ያየ ሰው ደግሞ በትክክል ነቢዩን በእውን እንዳየ ይቆጠራል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሕልሙን ያየው ሰው እቤቱ ውስጥ መኝታው ላይ ጀሃዲሊ ሆኖ ነው። ይህ ሁኔታ በዓለማዊ ጉዳዮች ውስጥ የሚሆን እስከሆነ ድረስ ከወዲያኛው ዓለም ጉዳዮች ጋር በተያያዘ መልኩ የማይቻልበት ምን ምክንያት ይኖራል?

ሟቹ የተቀበረበት መቃብር ቢከፈት መቃብሩ ስፋትም ሆነ ጥበት ሳያሳይ ልክ እንደነበረ ይታያል በሚለው አባባላቸው ላይ ለተመረኮዙት ከተለያየ አንጻር ምላሽ ይሰጣቸዋል።

<u>አንደኛ</u>:- ሸሪዓው ያረጋገጠውን ነገር እንዲህ ባሉ ተራ ውዥንብሮች መቃወም አይፈቀድም። ተቃዋሚው ሰው ሸሪዓው ይዟቸው የመጣቸውን እውነታዎች በሚገባ ቢያስተውል ውዥንብሮቹ ውዳቂ መሆናቸውን ይረዳል።

<u>ሁለተኛ</u>:- የመቃብር ዓለም ሕይወት (በርዘኽ) ጉዳዮች ከሕዋሳዊ ግንዛቤ ውጭ የሆኑና በሰው ግንዛቤ ሥር ሊውሉ የማይችሉ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች ከሰው ግንዛቤ ሥር የሚውሉ ቢሆኑ ኖሮ ከሕሳዊ ዕውቀት በራቀው (በጓይብ) ማመን ጥቅም የለሽ በሆነ ነበር። ባላዩት ነገር በሚያምኑ ምዕመናንና በክሐዲዎች መካከልም ልዩነት ባልኖረ ነበር።

<u>ሦስተኛ</u>:- የመቃብር ውስጥ ሥቃይና ደስታን የመቃብሩን መስፋትና መጥበብ መረዳት የሚችለው ሟቹ ብቻ ነው። ልክ አንድ ሰው ተኝቶ አስደሳችና ሰፊ ቦታ ውስጥ ሆኖ ወይም ጠባብና አስጨናቂ ቦታ ውስጥ ሆኖ በሕልሙ ሲመለከት እንደሚሆነው ማለት ነው። ሌላው ሰው የተኛው

ግለሰብ እቤቱ ውስጥ መኝታው ላይ እንደነበረ ምንም ለውጥ ያላሳየ መሆኑን ነው የሚረዳው። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአላህ (ሱ.ወ) ራእይ (ወሕይ) ሲተላለፍላቸው ከባልደረቦቻቸው (ከሰሓቦቹ) መካከል ሆነው ይሰሙ ነበር። ሰሐቦቹ ግን ምንም አይሰሙም ነበር። አንዳንድ ጊዜም መልአክ በሰው ተመስሉ ወሕዩን ያስተላልፍላቸዋል። ሰሐቦቹ ግን መልአኩን አያዩም፤ አይሰሙትም።

አራተኛ:- የሰዎች የግንዛቤ ደረጃ አላህ (ሱ.ወ) በሚሰጣቸው የግንዛቤ ደረጃ ብቻ የተገደበ ነው። ስለዚህ ሁሉንም ነገር ሊያውቁና ሊገነዘቡ አይችሉም። ሰባቱ ሰማያትና መሬት በውስጣቸው ያሉት ፍጥረታት በሙሉ አላህን (ሱ.ወ) ያጠራሉ፤ ያወድሳሉ። ይህን ውዳሴ አንዳንድ ጊዜ አላህ (ሱ.ወ) ከፍጡራኑ መካከል ለሻው ያሰማል። ይሁን እንጂ ይህ የፍጥረተ ዓለም ውዳሴ ከኛ ግንዛቤ ውጭ ነው። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ تسبح له السماوات السبع والأرض ومن فيهن، وإن من شيئ
إلا يسبح بحمده، ولكن لا تفقهون تسبيحهم﴾ الاسراء:٤٤

« ሰባቱ ሰማያትና ምድርም በውስጣቸውም ያለው ሁሉ ለርሱ ያጠራሉ፤ ከነገርም ሁሉ ከማመስገን ጋር የሚያጠራው ( የሚያወድሰው) እንጂ አንድም የለም፤ ግን ማጥራታቸውን አታውቁትም፤...»[109]

ሰይጣናትና ጋኔንም እንደዚሁ ምድር ላይ ይሄዳሉ ይመላለሳሉ። ጋኔኖች ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ቀርበው ነቢዩ የሚያነቡትን ቁርአን ካዳመጡ በኋላ ወደ ወገኖቻቸው ተመልሰው የሰሙትን መልክተ እስላም አስተ

109 አል- ኢስራእ /17/: 44
108 አል- ዙመር /39/: 42

ኣልፈጥል። ይህ ሁሉ ግን ከኛ ግንዛቤ ውጭ ነው። አላህ (ሱ.ወ) ይህንኑ በማስመልከት እንዲህ ብሏል:-

﴿ يا بنى آدم ليفتننكم الشيطان كما أخرج أبويكم من الجنة ينزع عنهما لباسهما ليرهما سوءاتهما، إنه يراكم هو وقبيله من حيث لاترونهم، إنا جعلنا الشياطين أولياء للذين لايؤمنون﴾

الأعراف:٢٧

« የአዳም ልጆች ሆይ! ሰይጣን አባትና እናታችሁን ሁፍረተ ገላቸውን ሊያሳያቸው ልብሶቻቸውን ከነሱ የገፈፋቸው ሲኾን ከገነት እንዳወጣቸው ሁሉ እናንተን አይሞክራችሁ! እነሆ እርሱ ከነሰራዊቱ ከማታዩዋቸው ሥፍራ ያዩዋችኋልና! እኛ ሰይጣናትን ለነዚያ ለማያምኑት ወዳጆች አድርገናል።» [110]

ሰዎች ሁሉንም የተፈጥሮ ክስተት ከግንዛቤያቸው ሥር ማዋል የማይችሉ እስከሆኑ ድረስም ከሕዋሳት የራቁና በሸሪዓው የተረጋገጡ ጉዳዮችን ለራሳቸው ስለማይገነዘቡ ብቻ ማስተባበል አይፈቀድም።

110 አል- አዕራፍ /7/: 27

## በቀደር ማመን

በ «ቀደር» ማመን አላህ (ሱ.ወ) በነባር ዕውቀቱና በጥበቡ መሠረት በተፈጥሮ ውስጥ የሚከሰቱ ክስተቶችን በሙሉ ጥንቱኑ ወስኖ ማስቀመጡን ማመን ማለት ነው።

## በቀደር ማመን አራት ነጥቦችን ያጠቃልላል

<u>አንደኛ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) ነገሮችን ሁሉ ከራሱ ሥራዎች ጋር የተያያዙትንም ሆነ ከፍጡራኑ ጋር የተሳሰሩትን በጥቅሉና በዝርዝር መጀመሪያና መጨረሻ በሌለው ሁኔታ የሚያውቅ መሆኑን ማመን።

<u>ሁለተኛ</u>:- ይህን ሁሉ አላህ (ሱ.ወ) በተጠበቀው ሰሌዳ (ለውሑል መሕፉዝ) ላይ የጻፈው መሆኑን ማመን።

እነዚህን ሁለት ነጥቦች አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ألم تعلم أن الله يعلم ما فى السماوات والأرض، إن ذلك فى كتاب، إن ذلك على الله يسير ﴾ الحج: ٧٠

« አላህ በሰማይና በምድር ውስጥ ያለን ሁሉ በእርግጥ የሚያውቅ መሆኑን አታውቅምን? ይህ በመጽሐፍ ውስጥ /የተመዘገበ/ ነው፤ ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።» [111]

ሙስሊም ዐብደላህ ብን ዐምር ብን አልዓስን በመጥቀስ በዘገቡት መሠረት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

كتب الله مقادير الخلائق قبل ان يخلق السما وات
والأرض بخمسين الف سنة >>

رواه مسلم

« አላህ የፍጥረታትን ወሳኔዎች ሰማያትንና መሬትን ከመፍጠሩ ከሃምሳ ሺህ ዓመት ቀደም ብሎ ነው የጻፈው ( የወሰነው)።» [112]

<u>ሦስተኛ</u>:- ከአላህ ሥራ ጋር የተያያዙም ሆነ ከፍጡራት ድርጊት ጋር የተያያዙ ክስተቶች በሙሉ በአላህ (ሱ.ወ) ፈቃድና በርሱ መሻት ብቻ የሚፈጸሙ መሆናቸው ማመን። አላህ (ሱ.ወ) ከራሱ ሥራ ጋር የተያያዘውን አስመልክቶ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وربك يخلق ما يشاء ويختار﴾ القصص:٦٨

﴿ ويفعل الله ما يشاء﴾ إبراهيم:٢٧

﴿ هو الذى يصوركم فى الأرحام كيف يشاء﴾ آل عمران:٦

« ጌታህም የሚሻውን ይፈጥራል፤ ይመርጣልም፤ ለነሱ (ለሰዎች) ምርጫ የላቸውም፤...» [113]

« ... አላህም የሚሻውን ይሠራል።» [114]

« እርሱ ያ በማሕጸኖች ውስጥ እንደሚሻ አድርጎ የሚቀርጻችሁ ነው።...» [115]

---

111 አል- ሐጅ /22/:70
112 ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ
113 አል-ቀሶስ /28/: 68
114 ኢብራሂም /14/: 27
115 አል-ዒምራን/3/:6

የፍጡራን ሥራ አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ولو شاء الله لسلطهم عليكم فلقاتلوكم﴾ النساء:٩٠

«.. አላህም ቢሻ ኖሮ በእናንተ ላይ ኃይል በሰጣቸውና በተጋደሉዋችሁም፤ »[116]

﴿ولو شاء الله ما فعلوه فذرهم وما يفترون﴾ الأنعام:١٢٧

«... አላህም በሻ ኖሮ ባልሠሩት ነበር፤ ከቅጥፈታቸውም ጋር ተዋቸው።»[117]

<u>አራተኛ</u>:- ፍጥረታት በሙሉ በማንነታቸው በባህሪያቸውና በአጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው ሁሉ የአላህ (ሱ.ወ) ፍጡራን መሆናቸውን ማመን። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿الله خالق كل شيئ وهو على كل شيئ وكيل﴾ الزمر:٦٢

﴿وخلق كل شيئ فقدره تقديرا﴾ الفرقان:٢

« አላህ የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ አስተናባሪ ነው።»[118]

«... ነገሩንም ሁሉ የፈጠረና በትክክልም ያዘጋጀ ነው።»[119]

ነቢዩ ኢብራሂም (ሰ.ዐ.ወ) ለሕዝባቸው የሰጡትን መልስ በመጥቀስ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿والله خلقكم وما تعملون﴾ الصافات:٩٦

---

116 አል-ኒሳእ/4/: 90
117 አል- አንዓም /6/: 137
118 አል-ዙመር /39/: 62
119 አል- ፉርቃን /25/: 2

« አላህ እናንተንም የምትሠሩትንም የፈጠረ ሲኾን፡፡ » [120]

ከላይ በገለጽነው መሠረት በቀደር ግመን አንድ ሰው በፍላጎቱ በሚፈጽማቸው ድርጊቶች ላይ ውሳኔና ችሎታ ያለው መሆኑን አይጻረርም። ሸሪዓውና ነባራዊ ሁኔታ የዚህን እንጻራዊ ነጻነት ወሳኝነት ያረጋግጡ ለታልና።

የሸሪዓውን ማረጋገጫ በተመለከተ ስለሰው ፍላጎት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ فمن شاء اتخذ الى ربه مآبا﴾ النبا

﴿ فأتوا حرثكم أنى شئتم] البقرة:٢٢٣

« .. የሻውም ሰው ወደጌታው መመለስን ይይዛል፡፡ » [121]

« ... እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ኹኔታ ድረሱ፤..» [122]

ችሎታን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ فاتقوا الله ما استطعتم واسمعوا وأطيعوا﴾ التغابن:١٦

﴿ لايكلف الله نفسا إلا وسعها، لها ماكسبت وعليها ما اكتسبت﴾

البقرة:٢٨٦

« አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት፤ ትእዛዙን ስሙም፤ ታዘዙም፤ ...» [123]

« አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፤ ለርሷ የሠራችው አላት። በርሷም ላይ ያፈራቸው (ኃጢአት) አለባት። ... » [124]

120 አል- ሷፋት /37/: 96
121 አል-ነበእ /78/: 39
122 አል- በቀራህ /2/: 223
123 አት-ተጋቡን /64/: 16
124 አል- በቀራህ /2/: 286

ነባራዊውን ማስረጃ በተመለከተ ደግሞ ማንኛውም ሰው በፍላጎቱ የመሥራት የመተው ነጻነትና መሻት ወይም ውሳኔና ፍላጎት ያለው መሆኑን ያውቃል። በፍላጎቱ የሚፈጽማቸውን እንደ መሄድ ያለውንና ከፍላጎቱ ውጭ የሚከሰተውን እንደ መንቀጥቀጥ ያለውን የሚለየውም በዚሁ የመሻት ነጻነት ነው። ይሁን እንጂ ያንድ ሰው ፍላጎት ወይም ማሻትና ችሎታው በአላህ (ሱ.ወ) መሻትና ችሎታ ብቻ የሚከሰቱ ናቸው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏልና:-

﴿ لمن شاء منكم أن يستقيم، وما تشاؤن إلا أن يشاء الله رب العالمين﴾ التكوير:٢٨ - ٢٩

« ከናንተ ቀጥተኛ መኾንን ለሻ ሰው (መገሠጫ ነው)። የዓለማት ጌታ አላህ ካልሻም አትሹም።» [125]

የኒቨርሱ በሙሉ የአላህ ንብረትና ግዛቱ በመሆኑ በግዛቱ ውስጥ ከርሱ ዕውቀትና መሻት ውጭ የሚሆን ምንም አይኖርም።

ከላይ በገለጽነው መሠረት በቀደር ማመን አንድ ሰው ግዴታዎቹን ለመተው ወይም ኃጢአት ለመሥራት ማመካኛና ማስረጃ ሊሆን አይችልም። ስለዚህም በዚህ ማመካኘቱ በተለያዩ መንገዶች ውድቅ ነው:-

<u>አንደኛ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ سيقول الذين أشركوا لو شاء الله ما أشركنا ولا آباؤنا ولاحرمنا من شيئ، كذلك كذب الذين من قبلهم حتى ذاقوا بأسنا

125 አል– ተክዊር /81/: 28– 29

قل هل عندكم من علم فتخرجوه لنا؟ ان تتبعون إلا الظن وان أنتم إلا تخرصون﴾ الأنعام:١٤٨

« እነዚያ ያጋሩት፣ አላህ በሻ ኖሮ እኛም አባቶቻችንም ባላጋራን ነበር፣ አንዳችንም ነገር እርም ባላደረግን ነበር፣ ይላሉ፣ እንደዚሁ (እነዚህ እንደሚሉ) እነዚያ ከበፊታቸው የነበሩት፣ ብርቱ ቅጣታችንን እስከ ቀመሱ ድረስ አስተባበሉ፣ ለኛ ታዛልቀልን ዘንድ (ማጋራታችሁን ለመውደዱ) እናንተ ዘንድ ዕውቀት አለን? ጥርጣሬን እንጅ ሌላ አትከተሉም፣ እናንተ ዋሾዎች እንጂ ሌላ አይደላችሁም በላቸው።» [126]

በቀደር (በአላህ መሻት) ማመካኘታቸው ተቀባይነት ቢኖረው ኖረው አላህ ቅጣቱን ባላቀመሳቸው ነበር።

<u>ሁለተኛ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ رسلا مبشرين ومنذرين لئلا يكون للناس على الله حجة بعد الرسل وكان الله عزيزا حكيما﴾ النساء:١٦٥

« ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር፣ አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የሆኑን መልክተኞች (ላክን)፣ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።» [127]

ቀደር ለአጥፊዎች (ለሕግ ተላላፊዎች) ማመካኛ አስረጅ ቢሆን ኖሮ መልክተኞች በመላካቸው ውድቅ ባልተደረገ ነበር። ከነቢያቱ መላክ በኋላ የተፈጸመው ጥፋትም በአላህ መሻት የተከሰተ ነውና።

126 አል- አንዓም /6/: 148
127 አል- ኒሳእ /4/: 165

ሦስተኛ:- ቡኻሪና ሙስሊም ዐሊይ ብን አቢ ጧሊብን በመጥቀስ የዘገቡት ቀጥሎ የተመለከተው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ:-

( ما منكم من أحد إلا قد كتب مقعده من النار أو من الجنة. فقال رجل من القوم: ألا نتكل يا رسول الله؟ فقال: لا اعملوا فكل ميسر، ثم قرأ) :

« ከናንተ መካከል መቀመጫው ከእሳት ውስጥ ወይም ከገነት ውስጥ ያልተጻፈ (ያልተወሰነ) አንድም ሰው የለም።» የአላህ መልክተኛ ሆይ! በዚያው በተወሰነው ላይ ተመርኩዘን እንቀመጥ ወይ? ብሎ ከተሰበሰበው መካከል አንድ ሰው ሲጠይቅ:- « የለም ሥሩ! ሁሉም ለተፈጠረለት ነገር የተገራ (የተመቻቸ) ነውና።»

አሉና የሚከተለውን የአላህ ቃል አነበቡ:-

﴿ فلما من أعطى واتقى] الليل:١٨

« ያ የሚጥራራ ችና ገንዘቡን (ለድሆች) የሚለግሰው።»[128]

በዚህም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሁሉም ሰው ግዴታውን እንዲፈጽም በግዜዝ በቀደር ማመካኘትን ከልክለዋል።

128 አል– ለይል /92/: 18

<u>አራተኛ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) ባሪያውን ይህን ሥራ ይህን አትሥራ ብሎ አዞታል። ያዘዘውም የሚችለውን ብቻ ነው። እንዲህ በማለት:-

﴿ فاتقوا الله مااستطعتم﴾ التغابن:١٦

﴿ لايكلف الله نفسا إلا وسعها﴾ البقرة:٢٨٦

« አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት፤ ... »[129]

« አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፤... »[130]

አንድ የአላህ ባሪያ በሥራዎቹ ላይ ተገዳጅ (ምንም የመሥራትና የመተው ነጻነት የሌለው) ቢሆን ኖሮ ሊወጣው የማይችል ከአቅሙ በላይ የሆነ ግዴታ በተጣለበት ነበር። ይህ ደግሞ መሠረት የሌለው ውድቅ ነገር ነው። ስለዚህም ባለማወቅ ወይም በመዘንጋት ወይም ተገዶ ኃጢአት ቢፈጽም ምክንያት አለውና አይጠየቅበትም።

<u>አምስተኛ</u>:- የአላህ ቀደር (መሻት) ነገሩ ከተከሰተ በኋላ ብቻ የሚታወቅ ድብቅ ምስጢር ነው። ያንድ ሰው ፍላጎት (ውሳኔ) አንድን ሥራ የሚቀድም በመሆኑ ያን ሥራ ለመሥራት ያለው ፍላጎት የአላህን ቀደር በማወቅ ላይ የተመሠረተ አይደለም። በዚህም በቀደር ማመካኘቱ ይወገዳል። በማያውቁት ነገር ማመካኘት ወይም የማያውቁትን በአስረጅነት ማቅረብ አይቻልምና።

<u>ስድስተኛ</u>:- የሰው ልጅ በዓለማዊ ጉዳዮቹ የሚስማማውን ለማግኘት ሲጓጓና የሚስማማውን ትቶ ወደማይስማማው የማይዞር መሆኑን እንመለከታለን። በዚህ በኩል በቀደር አያመካኝም። በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ውስጥ ግን ከሚጠቅመው ነገር ወደሚጎዳው ነገር በመዞር በቀደር ለምን ያመካኛል? ሁለቱ ነገሮች አንድ ዓይነት አይደሉምን?!

---

129 አል-ተጋቡን /64/: 16
130 አል- በቀራህ /2/: 286

ይህን የሚያብራራ ምሳሌ እነሆ:- አንድ ሰው ሁለት መንገዶች ኖርት አንደኛው ግድያ፣ ዝርፊያ ፣ የመብቶች መደፈር፣ ፍርሃትና ረሃብ ወደ ሰፈነበትና ሙሉ በሙሉ ሥርዓተ አልበኝነት ወደ ነገሠበት አገር የሚወስድ መንገድ ነው። ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ሥነ ሥርዓት ወደሰፈነበት፣ ጸጥታው የተረጋጋ፣ የተደላደለ ኑሮ የሚገኝበት የሰው ሕይወት ክብሩና ንብረቱ ወደሚከበርበት አገር የሚያደርስ መንገድ ነው። ከሁለቱ መንገዶች የትኛውን ነው የሚይዘው?

ሥነ ሥርዓትና ጸጥታ ወዳለበት የሚወስደውን መንገድ ነው የሚይዘው። ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው ሥርዓተ አልበኝነትና ስጋት ወዳለበት አገር የሚወስደውን መንገድ ይዞ በቀደር ሊያመካኝ በፍጹም አይችልም። ታዲያ በወዲያኛው ሕይወት (በአኺራ) ነገር የገነትን መንገድ ትቶ የእሳት ጎዳና በመምረጥ በቀደር ለምን ያመካኛል?

ሌላ ምሣሌ:- አንድ ሕመምተኛ መድኃኒት ይታዘዝለትና ሳይወድ በግድ ይጠጣዋል። ከሚጎዱት የምግብ ዓይነቶች ይከለከልና እያስፈለገውና ነፍሱ እየጓመጀች ይተወዋል። ይህ ሁሉ ለመዳንና ጤነኛ ለመሆን ሲባል ነው። በቀደር በማመካኘት ግን መድኃኒቱን ከመውሰድ አይታቀብም፣ ወይም የተከለከለውን ጎጂ የምግብ ዓይነት አይበላም። ታዲያ የሰው ልጅ አላህና ነቢዩ ያዘዙትን በቀደር በማመካኘት ለምን ይተዋል? የከለከሉትንም በቀደር በማሳበብ ለምን ይፈጽማል?

<u>ሰባተኛ</u>:- ግዴታዎችን በመተው ወይም ኃጢአቶችን በመፈጸም በቀደር የሚያመካኘው ሰው፣ ሌላ ሰው ጥቃት ፈጽሞበት ገንዘቡን ቢወስድበት ወይም መብቱን ደፍር በቀደር ቢያሳብብና አትውቀሰኝ ግፍ የፈጸምኩብህ በአላህ ቀደር ነው ቢለው ምክንያቱን አይቀበልም። ታዲያ ሌላ ሰው በጥለበት ግፍና የመብት መዳፈር ሁኔታ በቀደር ማሳበቡን የማይቀበል እስከሆነ ድረስ እሱ ራሱ የአላህን (ሱ.ወ) መብት ተጋፍቶ ቀደርን በማመካኛነት እንዴት ያቀርባል?!

የምዕመናን እናት ሁመር ብንት አልኸጧብ እጁ ሊቆረጥ የሚገባ ሌባ ተይዞ ቀረበላቸውና እጁ እንዲቆረጥ ያዛሉ። የምዕመናን እናት ሆይ! ይቆዩኝ! እኔ የሰረቅሁት በአላህ ቀደር ነው አላቸው። ዑመርም:- እኛም የምንቆርጠው በአላህ ቀደር ነው ማለታቸው ይነገራል።

## በቀደር ማመን ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል

<u>አንደኛ</u>:- ሳቢያዎችን በመመርኮዝ ለሥራ ሲነሱ፣ ሁሉም ነገር በአላህ ቀደር (ውሳኔ) ብቻ የሚፈጸም በመሆኑ በሳቢያዎቹ ብቻ ላይ ሳይተማመኑ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ መተማመን።

<u>ሁለተኛ</u>:- አንድ ሰው የፍላጐቱን አግኝቶ ሲሳካለት በራሱ ብቃት አለመኩራራትና አለመመጻደቅ። ስኬቱ ከአላህ (ሱ.ወ) በተገኘ ጸጋ እርሱ በወሰነው የድልና የበጐ ሳቢያዎች ውጤት ነውና። ራስን በራስ ማሞካሸትና ራሱን ማኩራራት ይህን የአላህ ጸጋ እንዳያመሰግን ያዘናጋዋል።

<u>ሦስተኛ</u>:-በአላህ መሻትና በወሳኔዎቹ (በቀደር) ከሚፈጸሙት ጉዳዮች አንጻር የሚወደው ነገር ስለአመለጠው ወይም የማያስደስት ነገር ስለደረሰበት ሳይጨነቅ እርጋታና የሕሊና ዕረፍት ማስገኘት።የሰማያትና የምድሩ ንግሥና የግሉ በሆነው አላህ ውሳኔ የተፈጸመና ወደድንም ጠላንም የግድ መፈ ጸም ያለበት ነገር ነውና። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:

﴿ ما أصاب من مصيبة فى الأرض ولا فى أنفسكم إلا فى كتاب من قبل أن نبرأها إن ذلك على الله يسير، لكيلا تأسوا على ما فاتكم ولا تفرحوا بماآتاكم والله لا يحب كل مختال فخور﴾

الحديد:٢٢ - ٢٣

«በምድርም፣ በነፍሶቻችሁም፣ መከራ (ማንንም) አትነካም፣ ሳንፈጥራት በፊት በመጽሐፍ የተመዘገበች ብትኾን እንጂ፤ ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።(ይህ ማሳወቃችን) ባመለጣችሁ ጸጋ ላይ እንዳታዝኑ፣ አላህም በሰጣችሁ ነገር (በትዕቢት) እንዳትደሰቱ ነው፤ አላህም ኩራተኛን፣ ጉረኛን ሁሉ አይወድም።»[130]

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ:-

( عجبا لأمر المؤمن ان أمره كله خير، وليس ذلك لأحد إلا لمؤمن إن أصابته سراء شكر فكان خيرا له، وان أصابته ضراء صبر فكان خيرا له) رواه مسلم

« የአማኝ (ሙእምን) ሰው ነገር አስደናቂ ነው። ሁሉም ነገሩ በጐ (መልካም ጉን ያለው) ነውና። ይህም የአማኙ (ባህሪ) እንጂ የሌላ የማንም አይደለም። የሚያስደስት ነገር ሲገጥመው (አላህን) ያመሰግንና ጥሩ ይሆንለታል። ክፉ ነገር ሲደርስበትም ይታገስና (ትዕግሥት) ጥሩ ይሆንለታል።»[131]

በቀደር ማመንን አስመልክተው ሁለት ቡድኖች ተሳስተዋል:-

<u>አንደኛው:</u>- አንድ የአላህ ባሪያ በሚሠራቸው ነገሮች ላይ የራሱ የሆነ ፍላጎትና ችሎታ (ኃይል) የሌለው ተገዳጅ ነው ያሉና «ጀበሪያ» በመባል የሚታወቅ ቡድን፤

<u>ሁለተኛ</u>:- አንድ የአላህ አገልጋይ በሚፈጽማቸው ሥራዎች ሁሉ የራሱ የሆነ ነጻ ፍላጎት (ውሳኔ) እና ኃይል ያለው ሲሆን፤ የአላህ (ሱ.ወ) ፍላጎት (መሺአህ) እና ችሎታው በግለሰቡ ተግባር ላይ ሚና (ተጽእኖ) የለውም የሚሉ «ቀደሪያ» በመባል የሚታወቅ ቡድን፤

---
131 ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

## ለመጀመሪያው ቡድን ለ «ጀበሪያ» የሚሰጥ የሸሪዓና የተጨባጭ እውነታ ምላሽ

<u>ሸሪዓን በተመለከተ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) አንድ አገልጋዩ ፍላጎት (መሺአህ) እንዳለው በማረጋገጥ ሥራውን ከሠሪው ጋር አያይዟል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿منكم من يريد الدنيا ومنكم من يريد الآخرة﴾

آل عمران:١٥٢

﴿وقل الحق من ربكم فمن شاء فليؤمن، ومن شاء فليكفر، إنا أعتدنا للظالمين نارا أحاط بهم سرادقها﴾ الكهف:٢٩

﴿من عمل صالحا فلنفسه، ومن أساء فعليها وما ربك بظلام للعبيد﴾ فصلت:٤٦

«... ከናንተ ውስጥ ቅርቢቱን ዓለም የሚሻ አለ፤ ከናንተ ውስጥም መጨረሻይቱን ዓለም የሚሻ አለ፤ ...» [133]

« :- እውነቱም፣ ከጌታችሁ ነው፤ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ፣ በላቸው፤ እኛ ለበደለኞች አጥሯ በነሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል፤ ...» [134]

« መልካም የሰራ ሰው ለነፍሱ ነው፤ ያጠፋም ሰው፣ በርሷ ላይ ነው፤ ጌታህም ለባሮቹ በዳይ አይደለም።» [135]

---

133 አል-ዒምራን/3/: 152
134 አል-ከሕፍ /18/: 29
135 ሐ.ሚም አስ-ሰጅዳህ /41/: 46

<u>ቷዉባዉዬን እውነታ በተመለከተ</u>:- ማንኛውም ሰው በራሱ ፍላጐት በሚፈጽማቸው እንደ መብላት፣ መጠጣት፣ መግዛትና መሸጥ ባሉት ድርጊቶቹና ከፍላጐቱ ውጭ በሚከሰቱት በወባ ምክንያት እንደ መንቀጥቀጥና ከጣሪያ መውደቅ በመሳሰሉት ድርጊቶች መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃል። በመጀመሪያው ሁኔታ ሳይገደድ በምርጫውና በፍላጐቱ አድራጊ ነው። በሁለተኛው ሁኔታ ደግሞ ድርጊቱ በምርጫውና በፍላጐቱ የተከሰተ አይደለም።

## ለሁለተኛው ቡድን ለ «ቀደሪያ» የሚሰጥ የሸሪዓና የአእምሮ መልስ

<u>ሸሪዓን በተመለከተ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) የማንኛውም ነገር ፈጣሪ ነው። ሁሉም ነገር የሚሆነው በርሱ መሻት (በመሺአው) ነው። የአገልጋይ ፍጡራት ሥራዎች የሚከሰቱት በርሱ ፍቃድና ፍላጐት መሆኑን በመግለጽ አላህ (ሱ.ወ) መጽሐፉ ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿ ولو شاء الله ما اقتتل الذين من بعدهم من بعد ماجاءتهم البينات، ولكن اختلفوا فمنهم من آمن ومنهم من كفر، ولو شاء الله ما اقتتلوا ولكن الله يفعل ما يريد﴾ البقرة:٢٥٣

﴿ ولو شئنا لآتينا كل نفس هداها، ولكن حق القول مني لأملأن جهنم من الجنة والناس أجمعين.﴾ السجدة:١٣

« ... አላህም በሻ ኖሮ፣ እነዚያ ከነርሱ (ከመልክተኞቹ) በኋላ የነበሩት፣ ግልጽ ታምራቶች ከመጡላቸው በኋላ ባልተጋደሉ ነበር፤ ግን ተለያዩ፤ ከነርሱም ውስጥ የካደ ሰው አለ፤ አላህም በሻ ኖሮ ባልተዋጉ (ባልተለያዩ) ነበር፤ ግን አላህ የሚሻውን ይሠራል።»[136]

« በሻንም ኖሮ ነፍስን ሁሉ ቅንነቷን (እምነቷን) በሰጠናት ነበር፤ ግን ገሀነምን ከአጋንንትና ከሰዎች የተሰበሰቡ ኾነው በእርግጥ እሞላለሁ፣ ማለት፣ ቃሉ ከእኔ ተረጋገጠ።»[137]

ለእምርጋን በተመለከተ:- ዩኒቨርስ በአጠቃላይ የአላህ ንብረት ነው። የዚህ ዩኒቨርስ አካል የሆነው የሰው ልጅም የአላህ (ሱ.ወ) ንብረት ነው። ተገኘው ንብረት ደግሞ በገኘው ባለንብረት ሀብት ላይ ከባለቤቱ ፍቃድና ፍላጐት (መሺአህ) ውጭ ሊያዝበት አይችልም።

## የእስላማዊ እምነት (ዐቂዳ) ዓላማዎች

የእስላማዊው እምነት (ዐቂዳ) ዓላማዎች ማለት ፍላጐቶቹና እምነቱን ከሚያዙ ጀርባ የሚያልሟቸው ውድ ግቦቹ ናቸው። ዓላማዎቹ ብዙና የተለያዩ ዓይነቶች ሲሆኑ ከነዚህም የሚከተሉትን እናገኛለን:-

አንደኛ:- ፍጹማዊ በሆነ ፍላጐት አላህን (ሱ.ወ) ብቻ መገዛት። እርሱ ሸሪክ የሌለው ብቸኛ ፈጣሪ በመሆኑ ዓላማንና መገዛትን (ዕባዳን) ለርሱ ብቻ ማድረግ ግዴታ ነው።

ሁለተኛ:- አእምሮና ፍካሬን ይህ ዐቂዳ ከልቦና በመጥፋቱ ምክንያት ከሚከሰተው ሥርዓተ አልባ መደናበር ነጻ ማውጣት። ልቡ ከዚህ እምነት ባዶ የሆነ ሰው ወይ ልቡ ከሁሉም ዓይነት እምነት ባዶ ሆኖ ተጨባጩን ቁስ

---

136 አል-በቀራህ/2/: 253
137 አል-ሰጅዳህ /32/: 13

አካል ብቻ የሚያመልክ ነው፡ ወይ ደግሞ በተሳሳቱ እምነቶችና አፈተረቶች ውስጥ የሚደናበር ነው።

<u>ሦስተኛ</u>:- የሕሊናና የአመለካከት ደስታ ማስገኘት። በዚህ ዐቂዳ ያመነ ሰው የሕሊና ጭንቀትም ሆነ የአመለካከት መምታታት የለበትም። ዐቂዳው አግኙን ከፈጣሪው ስለሚያገናኘው አቀናባሪ ጌትነቱንና ሕግ ሰጭ አስተዳዳሪነቱ ወዶ በመቀበል ልቡ በአላህ ውሳኔ (ቀደር) ይረካል። በእስላም ጸንቶ ሌላ መተኪያ የማይፈልግ ይሆናል።

<u>አራተኛ</u>:- አላህን በመግገዛት (በዕባዳና) ከሰዎች ጋር ባለው ማህበራዊ ግንኙነት ዓላማና ተግባርን ከስህተቶች ነጻ ማድረግ። ከእምነቱ መሠረቶች መካከል በመልክተኞች (በሩሱል) ማመን አንዱ በመሆኑና ይህም በተራው በዓላማም ሆነ በተግባር ንጹሕ የሆነውን ፈለጋቸውን መከተል ስለሚያጠቃልል ነው።

<u>አምስተኛ</u>:- በነገሮች ሁሉ ውስጥ ቁርጠኛና ትጉህ በመሆን፡ የመልካም ሥራ አጋጣሚን የአላህን ምንዳ /ሰዋብ/ በማሰብ ሳይጠቀሙ እንዳያመልጥ ማድረግ። የሚያስከትለውን ቅጣት በመፍራትም የኃጢአት አዝማሚያ ባዩ ቁጥር ከሥፍራው መራቅ። ከእምነቱ መሠረቶች አንዱ ደግሞ ከሞት ተቀስቅሶ በሠሩት ሥራ ዓይነት ተመጣጣኝ ዋጋ የሚሰጥ መሆኑን ማመን ነውና። አላህ /ሱ.ወ/ እንዲህ ብሏል:-

﴿ولكل درجات مما عملوا، وما ربك بغافل عما يعملون﴾

الأنعام:١٣٢

« ለሁሉም ከሠሩት ሥራ /የተበላለጡ/ ደረጃዎች አሏቸው፤ ጌታህም ከሚሠሩት ሁሉ ዘንጊ አይደለም።» [138]

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቀጥሎ በተመለከተ ሐዲስ ለዚሁ ዓላማ ገፋፍተዋል:-

---

138 አል- አንዓም /6/: 132

( المؤمن القوي خير وأحب إلى الله من المؤمن الضعيف، وفي كل خير أحرص على ما ينفعك واستعن بالله، ولا تعجز، وان أصابك شيئ فلا تقل لو أني فعلت كان كذا وكذا ولكن قل: قدر الله وما شاء فعل، فان لو تفتح عمل الشيطان) رواه مسلم

«ጠንካራ አማኝ ከደካማው አማኝ ይበልጥ አላህ ዘንድ በላጭና የተወደደ ነው። በሁሉም ዘንድ ደግ ነገር አለ። ለሚጠቅምህ ነገር ጓጓተህ (ተጣጣር) ከአላህ ረድኤት ጠይቅ። ደካማ አትሁን። አንድ ችግር ሲደርስብህ እንዲህ ባደርግ እንደዚያ ቢሆን ኖር እንዲህ በሆን ነበር አትበል። አላህ ወሰነ፡ እርሱ የሻውን ሥራ በል እንጂ። ‹ቢሆን ኖር› የሰይጣንን ሥራ ትከፍታለችና።»[139]

<u>ስድስተኛ</u>:- ሃይማኖቱን ለማረጋገጥና ግዕዛናቹን ለማጠናከር ማንኛውንም ውዱንም ርካሹንም ነገር ሁሉ ለሚሰዋ፡ በዚህ ረገድ ለሚደርስበት ችግር ግድ የሌለው ጠንካራ ሕዝብ መመሥረት። ይህን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ إنما المؤمنون الذين آمنوا بالله ورسوله ثم لم يرتابوا وجاهدوا بأموالهم وأنفسهم في سبيل الله أولئك هم الصادقون﴾ الحجرات:١٥

(እውነተኞዎቹ) ምእመናን፡ እነዚያ በአላህና በመልክተኛው ያመኑት፡ ከዚያም ያልተጠራጠሩት፡ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ የታገሉት ብቻ ናቸው፤ እነዚያ እነሱ እውነተኞቹ ናቸው።»[140]

---

139 ሙስሊም የዘገበት ሐዲስ
140 አል- ሑጁራት /49/: 15

<u>ሰባተኛ</u>:- ግለሰቦችንና ህብረተሰቦችን በማሻሻል ምንዳና ክፍያን ሁሉ በማቀናጀት በዛሬይቱ ቅርቢቱ ዓለምና በመጪው ዘለዓለማዊ ሕይወት ለተድላ መብቃት። ይህን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿من عمل صالحا من ذكر أو أنثى وهو مؤمن فلنحيينه حياة طيبة، ولنجزينهم أجرهم بأحسن ما كانوا يعملون﴾ النحل:٩٧

« ከወንድ ወይም ከሴት፣ እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሠራ፣ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፣ ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።» [141]

እነዚህ እንግዲህ ከእስላማዊ ዓቂዳ ዓላማዎች ከፊሎቹ ሲሆን አላህ (ሱ.ወ) ለኛና ለሙስሊሞች በሙሉ ዓላማዎቹን እውን እንዲያደርግልን እንመኛለን።

141 አለ- ነሕል /16/: 97